ጅማ ዩኒቨርስቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሑፍ አማርኛ

ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር


# አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅኦ (በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

አማርኛን ለማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

መታሰቢያ ታደሰ



ሐምሌ 2015 ዓ.ም

ጅማ

# አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶችን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅኦ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

መታሰቢያ ታደሰ

ዋና አማካሪ፡- ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

እና

ረዳት አማካሪ፡- ማንያለው አባተ (ዶ/ር)

ሐምሌ 2015 ዓ.ም

ጅማ

# ምስጋና

በቅድሚያ ይህ ጥናት እንደጀምር ቦታና ግዜአቸውን ሰውተው በየግዜው የማቀርብላቸውን ጽሁፍ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በጥልቅ በማየት ገንቢ አስተያየታቸውን ’ የጥናታዊ ጽሁፍን ምንነትና የአሰራር ስርዓትን እንድገነዘብ ለረዱኝ አማካሪዬ ለጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር) እና ማንያለው አባተ (ዶ/ር) ላቅ ያለ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

በጥናቱ አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ላደረጉልኝ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች’ ጽሁፍን በመተየብና ሙያዊ ምክር ለሰጡኝ እንዲሁም ስማቸዉን ለልጠቀስኳቸው በሃሳብ ለረዱኝ ጓደኞቼ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዕምሯዊ ማንበብን የመማር ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ለተማሪዎች በግልፅ በማስተማር ያለውን ሚና ለመመርመር ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የ2015 ዓ.ም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የነበሩ 75 ወንድ እና 75 ሴት በድምሩ 150 ተማሪዎች ሲሆኑ ጥናቱ መሰረት ያደረገውም ከፊል ሙከራዊ ዘዴ ናሙና ተመርጦ ተወስዷል። ከጥናቱ ተሳታፊዎችም በፅሑፍ መጠይቅ እና በፈተና መረጃዎች ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡትም መረጃዎች በT-test በSPSS software መረጃ መተንተኛ ተሰልተው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። ቅድሚያ በአዕምሯዊ ብልሃት ቀድመው ተምረው ስለነበር ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ምን ያህል ተገንዝበዋል የሚለውን ለማወቅ በድህረ-ትምህረት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል። ድህረ-ትምህርት ፈተናውም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ማለትም አዕምሯዊ ብልሃቶችን መማር አንብቦ ለመረዳት ያለውን ጠቀሜታ ከማሳየት አንፃር በቅድመ ልምምድ የሙከራ ቡድን የአንብቦ መረዳት ውጤት በአማካይ = 33.7 መደበኛ ልይይት = 0.48 ነው። በቅድመ ልምምድ የቁጥጥር ቡድኑ የአንብቦ መረዳት ውጤት ደግሞ አማካይ 33.8 ሲሆን በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት የተገኘው ደግሞ=1.6 ሲሆን የፒ ዋጋ $p>0.05$ ነው። ይህም የሚያሳየው በቅድመ ልምምዱ በሁለቱም ቡደኖች መካከል ልዩነታቸዉ የጎላ አለመሆኑን ነው። በድህረ ልምምዱ የሙከራ ቡድን የአንብቦ መረዳት ውጤትን ስንመለከት አማካይ = 40.4 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ = 10.01 ነው። በድህረ ልምምዱ የቁጥጥር ቡድን የአንብቦ መረዳት ውጤት አማካይ = 34.4 ነው። መደበኛ ልይይቱ = 7.1 ነዉ። በነፃ ናሙናቲ-ቴስት ሲሰላ =40.4 ሆኗል። በሁለቱ ቡድን መካከል የተገኘው የፒ ዋጋ $p< 0.05$ ሲሆን ይህም የፅሑፍ መረጃ ስታቲካዊ ስሌትም ከድህረ-ትምህርት ፈተናው ጋር ሲታይ (በ6) ነጥብ መብለጥን ያሳየ ሲሆን። ይኸውም አዕምሯዊ ብልሃቶችን መማር አንብቦ ለመረዳት ያለውን ጠቀሜታ አሳይቷል። በዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ መነሻ ሃሳብ በመውሰድ ወደፊት ቢደረጉ መልካም ናቸው የተባሉትን ሃሳቦች ለማቅረብ ያህል ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ የማንበብ ብልሃቶችን አቀናጅቶ ማስተማር የተሻለ ለውጥ እንደሚያመጣ የተገለጸበት ሁኔታ ስለአለ የጥናቱ ትኩረት የነበረው ብልሃቶችን በግልፅ ለተማሪዎች ማሰልጠን የሚል ስለሆነ ዕቅድ ተይዞ በቋሚነት በባለሙያ የተደገፈ ስልጠና ለመምህራን ቢሰጥ። ሌላው በዚህ ጥናት የተተገበሩትን ሳይሆን አጥኚዎች የምርምር ሂደቱን ቀይረው ማለትም አንብቦ የመረዳት ችግር ያጋጠማቸውን ተማሪዎች ተዛምዷዊ በሆነ መንገድ ለማጥናት ቢሞከር። በመጨረሻም በዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ ውስጥ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳትና በብልሃት አጠቃቀማቸው መሰረት በማድረግ መርምሮ ግኝቱን አንፀባርቋል በመሆኑም ለወደፊት ደግሞ ብልሃቶችን ከአንብቦ መረዳት ጋር በማያያዝ ፆታን መሰረት በማድረግ ቢጠና።

# የማውጫ ሰንጠረዥ

**ርዕስ** **ገፅ**


ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ ii

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር ........ 5

**1.3 የጥናቱ ጥያቄዎች** ........ 7

1.4 የጥናቱ አላማ ........ 8

1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 8

1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 8

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 8

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 9

1.7 የቁልፍ ቃላትናፅንሰ ሀሳቦች ብያኔ ........ 10

ምዕራፍ ሁለት ........ 11

ክለሳ ድርሳናት ........ 11

2.1 ፅንሰሀሳብ ቅኝቶች ........ 11

2.2 አዕምሯዊ የመማር ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለዉ ሚና ........ 11

2.3 ማንበብን የመማር ብልሀቶችና አከፋፈል ........ 13

2.3.1 አእምሮአዊ የማንበብ ብልሀት ........ 14

2.4 የአንብቦ መረዳት ምንነት ........ 17

2.5 የማንበብ ደረጃዎች ........ 18

2.5.1 የብልሃት ምንነት ........ 18

2.6 ማንበብን የመማር ብልሀቶችን ማስተማሪያ ዘዴ ........ 19
2.6.1 ማንበብን የመማር ብልሀት ማሰልጠኛ ሞዴል ........ 20
2.6.2. ጾታና ማንበብን የመማር ብሀቶች ........ 21
2.6.3 ማንበብን የመማር ብሀቶች አጠቃቀም ደረጃ ........ 21
2.7 የጥናቱ ንድፈሀሳባዊ ትውረት ........ 22
2.7.1 ታህታይ - ላዕላይ የማንበብ ሂደት ሞዴል ........ 24
2.7.2 የላዕላይ-ታህታይ የማንበብ ሂደት ሞዴል ........ 24
2.7.3 መስተጋበራዊ (interactive) የማንበብ ሂደት ሞዴል ........ 25
2.8 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 25
ምዕራፍ ሶስት ........ 29
የአጠናን ዘዴ ........ 29
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 29
3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ ........ 30
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 31
3.3.1 የፅሑፍ መጠይቅ ........ 31
3.3.2 ፈተና ........ 32
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 33
3.5 የጥናቱ ስነ-ምግባራዊ ሁኔታ ........ 34
ምዕራፍ አራት ........ 35
የጥናቱ ውጤት ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ ........ 35
4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና ........ 35
4.2 ጽሑፍ መጠይቅ አንድ ስልጠናውን ከመውሰዳቸው በፊት ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅናትንተና ........ 35
4.3 ተማሪዎች ስልጠናዉን ከመዉሰዳቸው በኂላ የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅናትንተና ........ 36
4.4 በፈተና የተገኘ ውጤትትንተና ........ 37

4.4.1 ከቅድመ -ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎችትንተና ........ 37

4.4.2 የድህረ-ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 38

4.5 የውጤት ትንትናው ማብራሪያ ........ 39

ምዕራፍ አምስት ........ 41

ማጠቃለያ፤መደምደሚያ እና የመፍትሄ ሃሳብ ........ 41

5.1 ማጠቃለያ ........ 41

5.2 መደምደሚያ ........ 42

5.3 የመፍትሄ ሀሳብ ........ 43

ዋቢ.ዎች (Reference) ........ 44

አባሪዎች ........ 47

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አእምሮአዊ ማንበብን የመማር ብልሀት የሚያየው አእምሮአዊ የሆኑ ሂደቶችን ሲሆን በቀጥታ የሚመለከተው መረጃዎችን ከትምህርት ስርዓት አንጻር ሲሆን ይኸውም፤ መረጃዎችን ለማግኘት፣ ለማስቀመጥ፣ ለመመለስ እና ለመጠቀም ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ይህ ብልሀት ተማሪዎቹ ወደፊት በቋንቋ ትምህርታቸው ሊያገኙ በሚችሉት አዲስ ጽንሰ ሀሳብ ላይ የተለያዩ ተግባራትን በመፈጸም በትምህርት ሂደቱ ላይ መነሳሳት እንዲያሳዩ እና በግለሰብ ደረጃ አንድን ጽሁፍ አንብበው እንዲረዱ የሚያደርጋቸው ብልሀት ሲሆን እንዲሁም ልእለ አእምሮአዊ ብልሀት ደግሞ ለተማሪዎቹ አቅጣጫ በማሳየት፣ የአንባቢዎችን የትርጉም መዋቅር በመገንባት፣ አንባቢዎች ነገሮችን በቅድመ ተከተል እንዴት እንደሚሰሩ እና የንባብ ሂደቱን እንዴት መቆጣጠር እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ እንደሆነ O'Malley and Chamot (1995)፣ Ratna (2014)፣Oxford (1990)፣ Israel (2007)፣William and Burden (1997) የገለጹትን በመገንዘብ ነው፡፡

በተጨማሪም እንደ Hedge (2000) አገላለጽ አእምሮአዊ ብልሀቶች ቀጥተኛ የቋንቋመማር ብልሀቶች ሲሆኑ ተማሪዎች በንቃት ከታላሚው ቋንቋ መልእክቶችን እንዲቀበሉ እና እንዲያፈልቁ ያስችላሉ፡፡ ስለሆነም በአእምሮአዊ ብልሀት እርዳታ አማካኝነት ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች ከአዲሱ መረጃ ጋር መገናኘት እንደሚችሉ እና አእምሮአዊ ብልሀቶችን በመጠቀም የተማሪዎችን የንባብ ግንዛቤ ማዳበር እንደሚቻል Baker & Brown (1984) እና Palinscar & Brown (1984) ያስረዳሉ፡፡

አዕምሮአዊ ብልሃቶች በአይነታቸው አራት የሚደርሱ ናቸው ከዚህ በታች እንደሚከተለው መግለፅ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ልምምድ ሲሆን ይህ ልምምድ ደግሞ ተማሪዎችን ከወቅታዊ ሁኔታጋር በቀጥታ እንዲገናኝ ሳይሆንከራሳቸው ቅድመ ዕውቀት እንዲነሱ ማድረግ ነው፡፡ሁለተኛው ደግሞ ማሳጠር ነው ይህ ደግሞ የተማሪዎችን ችሎታ ማሻሻልና ትምህርቱ በአእምሯቸው ውስጥ ለረዥም ጊዜ አይረሴነት እንዲኖረው እንዲሁም በትምህርቱና በአስተማሪው መካከል አዳዲስ መረጃን ከቅደመ ዕውቀታቸው ጋር ለማያያዝ ይረዳል፡፡ሶስተኛው ማጠቃለል የሚለው ሲሆን በዘህ ውስጥ ተማሪዎች አስፈላጊና የሚመጥናቸውን መረጃዎችን የሚመርጡበትና የሚያገናኙበት ሂደት ነው፡፡ አራተኛው ደግሞ ትንተና የሚል ነው ይኸውም የተማሪዎች ቅድመ ዕውቀቶች በተግባር የሚታዩበትና

በመንገዳቸው ላይ የሚፈጠሩ አዳዲስ ችግሮችንናሁኔታዎችን ለመፍታት ይረዳቸዋል (Rebecca Oxford 2001)::

ማንበብ ማለት አንድን ጽሑፍ በትክክል አንብቦ መረዳት ወይም ጸሀፊው ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በትክክል መገንዘብ ማለት ነው፡፡ ማንበብን በሚመለከት Conley (1992) እንደገለፁት ማንበብ ማለት በማንበብ ተግባር ላይ በፀሀፊው እና በምንባቡ ውስጥ ከቀረበው አዲስ መረጃና አውድ ጋር በአንድነት አዋህዶ የፅሑፉን ሙሉ መልዕክት በሚገባ መረዳትን የሚመለከት ነው፡፡

እንደ Harmer (1991) አገላለፅ የማንበብ ክሂል ከተቀባይ ክሂሎች የሚመደብ ሲሆን ከሚነበበው ፅሁፍ ውስጥ መልዕክቱን መረዳት፣የጸሁፉን ዝርዝር ሃሳብ መለየትን፣ አዳዲስ መረጃዎችን መቀበልናማንጸባረቅ፣የፅሑፉን አወቃቀርና አደረጃጀት በሚገባ ማስተዋልና መገምገምን፣ በፅሁፉ ውስጥ ያሉ አውዳዊ አመለካከቶችን ፋይዳ መረዳትንና ሌሎችንም ጉዳዩች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ አንብቦ መረዳት ደግሞ አንባቢው የተለያዩ ብልሃቶችን ተጠቅሞ ፅሁፉን መልዕክት ለመረዳትና ለመገንዘብ ያለው ችሎታ ነው፡፡ አንብቦ መረዳት የአንባቢው ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችንና ስልቶችን መጠቀም አለባቸው Harmer (1991)፡፡

አንብቦ መረዳት የአንባቢው ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የተለያዩ የማንበብ ብልሃቶችንና ስልቶችን መጠቀም አለባቸው (Harmer፣1991) ፡፡እንደBloock (1986) አገላለፅ ማንበብና አንብቦ መረዳትን በሚመለከት የተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ፍልሰፍናዎችን አንፀባርቀዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ቅድሚያውን የሚይዘው ባህሪያውያን ፍልስፍና ነው፡፡ ይህ ፍልስፍና በተለይም በ1920ቹ ጀምሮ እስከ 1960ዎቹ ድረስ ባሉት ጊዜያት በስነ-ትምህርትና በስነባህሪ ዘርፎች ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘ ነበር፡፡በባህሪያዊያን ፍልስፍና መሰረት የማንበብ ሂደት

አእምሯዊና ባህሪያዊ ክስተት ተደርጎ የሚቆጠር ሲሆን በዘመኑ የተካሄዱ ምርምሮችም ትኩረታቸው አንብቦ መረዳት ሊታይና ሊዳሰስ የሚችል ነው በማለት ገልፀውታል፡፡ከባህሪያዊያን ፍልስፍና አንፃር አንብቦ መረዳትን ለማከናወን ዋነኛ ተተኳሪ ወይም አስፈላጊው ነገር የሚነበበው ፅሁፍ ነው፡፡ በመሆኑም አንባቢው የቀረበለትን ፅሁፍ በማንበብ እያንዳንዱን ፊደላትና ቃላት ትርጉም መፈለግና መስጠት ላይ እንዲያተኩር ይፈለጋል፡፡መረዳት የሚፈጠረውም በፅሁፉ ውስጥ የተካተቱትም እያንዳንዱ ቅንጣት ትርጉም በቅድሚያ ማወቅ ሲቻል ነውእንድሪስ (2000) (Laberg& Samuel 1997) ጠቅሶ እንዳቀረበው ፡፡እንደ ባህሪያዊያን ትውረታዊ አተያይ መማር የባህሪ ምስረታ ሲሆን

ድግግሞሽ፣ማነቃቃት እና ምላሽ መስጠት ለቋንቋ መማር ወሳኝ ተግባራት እንደሆኑ ያስረዳሉ (Omaggion 1993):: በባህሪያዊያን አተያይ መሰረት የማንበብ ሂደት ከእይታ መረጃ ማግኘት ማለትም ከተሰጠ ምንባብ ፊደልና ቃላትን መለየት ፣አንባቢን በማነቃቃት ፍችን መልሶ ማዋቀር እና መገንዘብ ያስችላል የሚል ነው(newby 2013):: በባህሪያዊያን አመለካከት አንድን ፅሁፍ ለማንበብና ለመተርጎም ከመስመራዊ ዕድገት የሚጀምርና በስነ-ትርጉም ውክልና የሚጨርስ ተደርጎ ይወሰዳል(Ling 2011)::

የማንበብ ትምህርት ታሪካዊ አመጣጥ በመስኩ ያሉ የስነልሳን ባለሞያዎች በሁለት ዋና ጊዚያት ከፍለው አስቀምጠውታል Cnond (2016) ገለፃ መጀመሪያው ዘመን የጀመረው 1940ዎቹ ሲሆን በወቅቱ እነ Bloomfield (1942) and Fries (1962) የተባሉ የስነልሳናዊ ምሁራን ማንበብ ማለት የቋንቋን ምልክቶች የመለየት ተግባር ነው። ይህውም ምስሎችን ከሚታየው ምልክታቸው ጋር ማዛመድ ማለት እንደሆነም እኒህ ምሁር አክለው አስርድተዋል Tylor and Norbush (1983) ቃላዊ ወይም አፋዊ ንባብ በማለት ሲገልፁት Nutall (1986) ደግሞ ድምፅ በማሰማት ማንበብ የሚለውን ስያሜ ስጥተዋል::

Hoang (2016) Saenger (1997) ዋቢ አድርገው እንደሚገልፁት 2ኛው ዘመን የጀመረው 1960ዎቹ ሲሆን ወቅቱም ዝምታ ወይም ድምፅ ሳያሰሙ ማንበብ ጠቀሜታ እንዳለው በአብዛኛው ስነ-ልቦናዊያንና ስነልሳናዊያን ትኩረት የሰጡበት ወቅት ነበር። የHoang (2016) ማጠቃለያም ማንበብ በሁለት ዋና ዋና ፈርጆች የተከፈለ ሲሆን እነሱም አፋዊ/ቃላዊ/ንባብ እና ድምፅ ሳይሰሙ ማንበብ ናቸው በሚል ነበር 1960ዎቹ አካባቢ የትርጉም ምንነትና ብያኔ እንዲሁም ፅንስ ሀሳብ በስፋት ተቀባይነትን አግኝቶ የአብዛኛዎቹን ተመራማሪዎች ትኩረት ለመሳብ የምርምር ስራዎችንም እንዲያካሂዱ መንገድ ከፍቷል።

ከዛ በተወሰደዉ ልምድም እንደየተማሪዎች የክፍል ደረጃ በይዘትና በአቀራረቡ ተመጥኖ የመማሪያ ና የማስተማሪያ መፅሀፍት እንዲሁም መርሃ ትምህርት ተዘጋጅቶ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች መሰጠት ተችሏል።

የባህሪያውያን አተያይ ታህታይና-ላዕላይ ተብሎ በሚታወቀውና እስከ 1960ቹ ድረስ ባሉት አመታት ከፍተኛ ተቀባይነትን አግኝቶ በነበረው የማንበብ ሞዴል ከፍተኛ ተፅጽኖ አሳርፏል። ይህን የማንበብ ሞዴል ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቁት Goff (1972) የተባሉ ምሁር ናቸው። በታህታይ-ላዕላይ የማንበብ ሞዴል መሰረት ማንበብ ባለአንድ አቅጣጫ

ሲሆን ከሚነበበው ፅሁፍ በመነሳት ወደ አንባቢው የሚጓዝ ነው፡፡በዚህ የማንበብ ሞዴል ትርጉም ያለው ነገር ሁሉ የሚገኘው ለንባብ በቀረበው ፅሁፍ ውስጥ ነው፡፡

አንብቦ መረዳት የሚፈጠረውም በቅድሚያ በእያንዳንዱ ቃላት ውስጥ የሚገኙ ድምፆችንና ፊደላትን በመለየትና ለነዚህ ቃላት ትርጉም በመስጠት ነው፡፡ይህ በቃል ደረጃ የሚከናወን የመረዳት ሂደትም ውስብስብ የሆኑ ፅንሰ-ሃሳቦችን ለመገንዘብ ወይም አጠቃላይ ፅሁፉን ለመረዳት መንገድ ይከፍታል (Davis 1995)::

ከ1960ቹ መጠናቀቂያ ጀምሮ በስነ-ልቦናና በስነ-ትምህርት ፍልስፍና ዘርፍ የአመለካከት ለውጦች ከመከሰታቸው ጋር ተያይዞ የባህሪያውያን ፍልስፍና ላይ የተለያዩ ትችቶች እየተነሱ ሄዱ፡፡ ከባህሪያውያን ንድፈ-ሃሳብ የተለዩ ጽንሰ-ሃሳቦችንየሚያራምዱ ፍልስፍናዎች ብቅብቅ ማለት ጀመሩ፡ ፡በወቅቱ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ የመጣውም የግንባታውያን ንድፈ-ሃሳብ ነው፡፡በግንባታውያን ንድፈ-ሃሳብ አራማጆች አመለካከት መማር ማለት ለነገሮች ትርጉም የመፍጠር ሄደት ሲሆን የሚከሰተውም በተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ ነው፡፡ ይህ ንድፈ-ሃሳብ በጊዜው ከማንበብ ጋር ተያይዘው የተካሄዱ የምርምር ውጤቶች ላይ ከፍተኛ ተጽኖ መፍጠር ችሏል (Carrell 1998)::

Harmmer (1994:16-18) እንዳሉት ማንበብ ከአራቱም መሰረታዊ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን መቀበያ ክሂል (Recepttive skill) በመባል ይጠራል፡፡በሌላ በኩል ማንበብ ማለት አንድን ፅሑፍ የመረዳት የመተርጎምና ተገቢውን (የምንፈልገውን) የተላለፈውን መረጃ የመውሰድ ሂደት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ ከገለፃው መረዳት እንደሚቻለው ማንበብ ግላዊ ሂደት ስለሆነ በዚህ ግላዊ ሂደትም በጊዜና በቦታ ከእኛ ርቆ ከሚገኝ ከአንድ ፀሀፊ መልዕክት ልንቀበል እንችላለን የተቀበልነውን መልዕክት የሚሳድርብን ስሜት ወይም ለመልዕክቱ የምንሰጠው ምላሽ ሌሎች በቀጥታ ሊያስተውሉት ወይም ላያስተውሉት ይችላሉ፡፡ ማንበብ በአብዛኛው ትምህርትቤት ሳይገባ የሚለመድ ክሂል አይደለም፡፡ ሰዎች ማንበብን የሚማሩትና ትምህርትቤቶች የማንበብ ትምህርት ሰፊ ቦታ የሚሰጠው ሆኖ ይገኛል፡፡ ዘውዱ (2008) (Brown፣1996)ን ጠቅሶ እንደገለጸው አንዳንድ የምርምር ውጤቶችም የትምህርትቤቶች መሠረታዊ ሀላፊነት ተማሪዎችን ማንበብ ማስተማር እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡ ትምህርት ቤቶች ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች የማንበብ ክሂላቸው ዳብሮ ዕውቀታቸውን ሊያሳድጉ ይገባል፡፡ ይህን ማድረግ ከተሳናቸው ግን ትምህርትቤቶችም ሆኑ ተማሪዎች ውጤታማ ናቸው ሊባሉ አይችሉም፡፡ ባጠቃላይ ከላይየተገለፀው ዳራ ከተማሪዎች አንብቦ መረዳት አንፃር የተለያዩ ምሁራን ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን ሰንዝረዋል በመሆኑም

ሁሉም የምሁራን ሃሳቦች በርግጥ ጠቀሜታቸው የማያጠራጥር ቢሆንም በዚህ ጥናት ውስጥ ግን ለአንብቦ መረዳት የተለያዩ ጠቀሜታዎች ያላቸውን፣በብልሃቶች ዙሪያ ብልሃቶችን ከመጠቀም የሚገኙትን ተለያዩ ፋይዳዎች በሚመለከት እንዲሁም በአንብቦ መረዳት ዉስጥ ብልሃቶችን በመጠቀም ያለውን አስተዋፅኦ ሲያጎሉ ይችላሉ የተባሉትን ሀሳቦች የሰነዘሩ ምሁራን ሀሳባቸው ተካቶበታል፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

በአለም አቀፍ ደረጃ በአእምሮአዊ ብልሀቶች እና በአንብቦ መረዳት ችልታ መካከል ያለውን ግንኙነት በጥናት ለማሳየት በተለያዩ ጊዜያት ሙከራዎች ተካሂደዋል፡፡ ለምሳሌ፤ Marley et al. (2010)፣ Ozek and Civelek (2006)፣ Aghaei (2011)፣ Sahan (2012) እና Ratna (2014) አእምሮአዊና የማንበብ ብልሀቶች አንብቦ የመረዳት ችልታን ለማዳበር እንደሚያስችሉ ሲያስረዱ፤ በተመሳሳይ Yohannes (2013) በእንግሊዘኛ ትምህርት ላይ ባደረጉት ሀገረኛ ጥናትም ከአጠቃላይ የማንበብ ብልሀት ማለትም አእምሮአዊ ብልሀቶችን በመውሰድ የአሰሳ ጥናት ያደረጉ ሲሆን፣ መምህራኑ ስለብልሀቶቹ የተወሰነ ግንዛቤ ቢኖራቸውም በመማሪያ ክፍል ውስጥ እንደማይተገብሩት፣ተማሪዎቹ ግን በብልሀቶቹ ለመማር ከፍተኛ መነሳሳት እና የመማር ፍላጎት እንደታየባቸው በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡

በተለያዩ ይዘቶችና ቦታዎች ብልሃቶች መማር ዘሪያ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ለምሳሌ፤ AbManan et al. (2011) ቋንቋን የመማር ብልሀትእንግሊዘኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በሆኑ የኮላጅ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት አእምሮአዊ፣ ትውስታ፣ ማካካስ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ማህበራዊ ብልሀቶችን በመጠቀም ተማሪዎችን በሙከራና በቁጥጥር ቡድን በመክፈል የሙከራ ቡድኑ በብልሀቶቹ ልምምድ ያደረጉ ሲሆን፣ በብልሀቶቹ የተማሩ ተማሪዎች ካልተማሩት የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገቡ ያስረዷሉ፡፡

በሀገራችን የቋንቋ ትምህርት አውድ በተማሪዎች ላይ ከሚታዩ ችግሮች አንዱ ተማሪዎች እንዴት እንደሚያነቡ አለማወቅ እንደሆነም ይጠቀሳል፡፡ ተማሪዎች እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ባለመማራቸው አንብቦ የመረዳት ችግራቸው የጎላ ነው፡፡ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችግር ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት የሚል ጥያቄ ሲነሳ ችግሩን ለማስወገድ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ የማንበብ ብልሃቶችን ማስተማር ይገባል የሚሉ ወገኖች አሉ (Tesfu 2015፣ Belilew 2015፣ Solomon 2000፣ Dawit 2014)፡፡

ተማሪዎች የማንበብ ትምህርትን በሚማሩበት ጊዜ በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተገለፁ የችሎታ መለኪያ በግልፅ የተቀመጠ ሲሆን፤ አንድን ፅሁፍ አንብበዉ የቃላትን ተግባር በምክንያትና ውጤት የተደራጁትን ሀሳቦች በማስረጃ መግለፅ፣ ስለተለያዩ ውስብስብ ነገሮች አሰራርና አጠቃቀም የሚገልፁ ፅሁፎችን አንብበው የተረዱትን በትክክል መግለፅ ፣እያነበቡ ካለው ምንባብ ውስጥም ቀጣይ ሀሳቦችን መተንበይ፣በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ቃላት እንደ አገባባቸው ሊሰጡ የሚችሉትን ፍች ማሳየት ፣ካነበቡት ምንባብ በመነሳት የራሳቸውን ድምዳሜ መስጠትና ለድምዳሜያቸውም መሰረት የሆኑትን ካነበቡዋቸው ግላዊ ፅሁፎች ውስጥ መጥቀስና ማቅረብ ናቸዉ (የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት እና የሚጠበቅ የአጥጋቢ ችሎታ ብቃት ደረጃ (2004)፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ምንም እንኳን ከተማሪዎችየሚጠበቅ ችሎታ ቢኖርም ተማሪዎችግን አንብበው ለመረዳት እንደሚቸገሩና በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ተግባር በጊዜና በሰዓቱ ለማከናዎን አስቸጋሪ የሆነበት መንገድ አጥኚዋ ካሁን በፊት በምታስተምርበት በረዥም ጊዜ የስራ ሂደትማየት ተችሏል፡፡ ይህም ለጥናቱ መነሻ እንዲሆን አጥኚዋን ገፋፍቷታል፡፡

Jhonson (2008)፡፡ በበኩላቸው ማንበብን ማስተማር ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገው ማንበብን ለመማር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ጭምር እንደሆን ይገልፃሉ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ማንበብን ለመማር የሚያስችሉ ሁኔታዎች ከተመቻቹላቸው በአግባቡ ሊማሩና ክሂሉን ሊያዳብሩ ስለሚችሉ እንደሆንና ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታም በትምህርትቤት ህይወት እጅግ መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ Nunan (1991) & Messi (1997) ያስረዳሉ፡፡ AbMananetal(2011) ቋንቋን የመማር ብልሃት በአፍመፍቻ ቋንቋቸው በማስተማር በተቋም ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ብልሃቶችን ተጠቅሞ በሙከራና በቁጥጥር ቡድን በመክፈል በሙከራ ቡድኑና በብልሃቶች ልምምድ ያደረጉ ሲሆን በብልሃቶች የተማሩ ተማሪዎች ካልተማሩት የተሻለ ውጤት አንዳስመዘገቡ በጥናታቸው ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም ብልሃቶችን ስለመማር አስፈላጊነት በተመለከተ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በብልሃቶች ትምህርት በመታገዝ ማዳበር አስፈላጊ እንደሆነ (oxford 1990) እና Anderson (1991)ያስረዳሉ፡፡ ለማዳበርያላቸውን ሚና ለመፈተሽ ምርምራቸውን አከናውነዋል፡፡ በምርምራቸው የሁለት ቡድን ነፃ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (Independent samples t-test) ተጠቅመው ባደረጉት ትንተና ግኝትም የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድኅረትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ድኅረትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዳለው አረጋግጠዋል፡፡

Oxford1990)እና Anderson(1991) ብዙጥናቶች ብልሀቶችን በመማር በኩል የተሰሩ ቢሆንም አከራካሪ ጉዳዮች ይኖራሉ ሆኖም ከተጠኑት ጥናቶች ዉስጥም ብልሀቶችን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመርዳት ችሎታን በማዳበር በኩል አስፈላጊ እንደሆነ (Oxford 1990) እና Anderson(1991) ገልፀዋል በሀገራችን በኩልም ረእሶቹ የተለዩ ይሁኑ እንጅ ሁለት የሀገር በቀል ጥናቶችንለምሳሌ ሰርካለም (2010) እና ደመቁ (2011) ስመለከት ብልሀቶችን በማስተማ ርአመርቂ ባይባልም እስካሁን ከነበረዉና ከተለመደዉ አሰራር የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገበ የገለፁበት ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ Barnett (1988) የማንበብ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉን ጠቀሜታ በተመለከተ ባደረጉት ጥናት የብልሃት ስልጠና ከተሰጣቸ ይልቅ ስለ አንብቦ መረዳት ብልሃቶች ምንነት ሳይማሩ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን በተከታታይ እንዲሰሩ የተደረጉ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ስለ ብልሃቶቹ ጠቀሜታ ከተማሩት የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ መሆኑን ገልፀው የታየው ልዩነት ግን የጎላ እንዳልሆነ ጠቁመዋል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የተለያዩ ብልሃቶች አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ምን አስተዋፅኦ እንዳላቸዉ በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ድምዳሜዎችን አስቀምጠዋል ፡፡ስለዚህ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደተማሪው ሁኔታ ሊለያይ ይችላልና በዚህ ጥናትም በብልሃቶች አንብቦ መረዳትን ማስተማርውስጥ ምን አይነት ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል አጥኝዋን ካነሳሳት ውሰጥ ሌላኛው ምክንያት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጥያቄዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አእምሯዊ ብልሀቶችን በግልጽ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ሲሆን ይህንን ለማሳካት ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይዞ ተነስቷል፡፡

- አዕምሯዊ ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያሻሽላልን?
- አዕምሯዊብልሃቶችንበግልፅ ከተማሩ በኋላ የተማሪዎች የብልሀት አጠቃቀም ደረጃ ተሻሽሏልን?

## 1.4 የጥናቱ አላማ

### 1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ አዕምሯዊ ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነዉ፡፡

### 1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ከላይ የተጠቀሰውን የጥናቱ ጥያቄዎች በመነሳት ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

- አዕምሯዊ ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን መሻሻል አለመሻሻሉን መፈተሽ፡፡
- አዕምሯዊ ብልሃቶችን በግልፅ ከተማሩ በኂላ የተማሪዎች የብልሀት አጠቃቀም ደረጃ መሻሻላቸዉን ለመፈተሽ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ተማሪዎች በማንበብ ተግባር የሚታዩባቸውን ተላውጦዎች መለየት ለመማር-ማስተማሩ ሂደት የላቀ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ በመሆኑም በዚህ መልኩ ሙከራዊ ምርምር ተደርጋል፡፡ ውጤቱም የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ሊኖሩት እንደሚችል ይታመናል፤

- የቋንቋ ሥርአተ ትምህርትና የማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የአንብቦ መረዳትን ችሎታና የማንበብን ፍላጎት ለማሳደግ የሚያስችሉ ማንበብን የማስተማሪያ ዘዴ አዕምሯዊ ብልሃቶችን እንዲያካትቱ ጊዜ በመቆጠብ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡
- ማንበብን የማስተማሪያ ዘዴ አዕምሯዊ ብልሃቶች አንብቦ የመረዳትን ችሎታና የማንበብን ፍላጎት ለማሳደግ ያላቸውን ሚና በተመለከተ የተማሪዎችንና የመምህራንን መማር ማስተማሩን በማስተካከል(በማሳደግ)፣ ለትግበራ በማነሳሳት ጠቀሜታ ላይ ይውላል፡፡
- በአዕምሯዊ ብልሃቶች መካከል አንብቦ የመረዳትንና ማንበብን በማሳደግ ሂደት ለተማሪዎች የበለጠ ጠቃሚ የሆኑትን ለመለየት ያስችላል፡፡
- በአዕምሯዊ ብልሃቶች መካከል አንብቦ የመረዳት ሂደትን ለመተግበር የበለጠ ከባድ የሆኑትን በመምሪጥመምህራን የትኛውን መተግበር እንዳለባቸው ለመለየት ያስችላል፡፡
- በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታንና ማንበብን በተመለከተ ለሚደረጉ ሌሎች ጥናቶችና አጥኚዎች እንደ መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በ2015 ዓ.ም በኦሮሚኣ ክልል፣ በጅማ ዞን በቀርሳ ወረዳ በቡልቡል ከሚገኙ አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርትቤቶች ላይ ትኩረቱን አድርጎ ነው፡፡ ከክፍል ደረጃና ከተማሪዎች አንፃርም የክፍል ደረጃው በዓላማ ተኮር ናሙና፣ እንዲሁም በቀላል የዕጣ ናሙና በተመረጡ በቡልቡል ከሚገኙ አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርትቤቶችና አምስት የመማሪያ ክፍሎች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡ ከብልሃቶች አንፃር ደግሞ ጥናቱ የአዕምሯዊ ብልሃቶች የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና ማንበብን ለማሳደግ የሚኖራቸውን ሚና በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነዉ፡፡ ይኸውም በመጀመሪያዉ ሳምንት መደጋገምና መዘርዘር የሚሉት ሲሆኑ በሁለተኛ ሳምንት ደግሞ ምክንያታዊ መሆን የሚለውን በሶስተኛዉ ሳምንት ደግሞ መመርመር በአራተኛው ሳምንት መገመት በአምስተኛው ሳምንት ማለማመድ ሲሆን በስድስተኛዉ ሳምንት ደግሞ ማስተዎስና መከታተል የሚሉትን የአእምሯዊ ብልሃት ተግባራት ለተማሪዎች የንባብን አውድ በማቅረብና በግልፅ በማሰልጠን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሻሻል እና ለብልሃት አጠቃቀማቸው የሚኖረውን አስተዋፅኦ የሚመረምር እንዲሆን ታልሞ ስልጠናው ለተማሪዎች ይሰጣል፡፡ በመሆኑም ዘዴው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና ማንበብን ለማሳደግ የሚኖረውን ፋይዳ በተናጠል ይመረምራል እንጂ በአንብቦ መረዳትና ማንበብን መካከል ያለውን ተዛምዶ አይፈትሽም፡፡ አዕምሯዊ ብልሃቶቹም በውህደት እንጂ በተናጠል ለአንብቦ መረዳትም ሆነ ለማንበብ ተነሳሽነት የሚኖራቸውን ፋይዳ አይመለከትም፡፡ በተጨማሪም የአዕምሯዊ ብልሃቶች በተማሪዎች በኩል የአጠቃቀም ደረጃና የጠቃሚነት ሁኔታ እንዲሁም የክብደት ደረጃ ይፈትሻል፡፡ ከብልሀቶች ዉስጥም አምሯዊ ብልሀቶች ማሰልጠን የአማርኛ ቋንቋን አንብቦ የመርዳት ችሎታን በማሳደግ በኩል ያለውን አስተዋፅኦ በመፈተሽ ላይ ያተኮር በመሆኑ ብልሀቶቹም በሚተገበሩበት ጊዜ ሁሉንም በአንድ ክፍለ ግዜ ሳይሆን በተለያዩ ጊዜ እያቀረቡ እንዲጠቀሙበት በማድረግ ነዉ ፡፡ይህም ማለት በየጊዜዉ ብልሀቶችን እየመረጡ ከምንባቡ ይዘቶች ጋር በማያያዝ እና በማስተማር ለተማሪዎች የአንብቦ መርዳት ችሎታ ላይ ጥሩ ውጤት መምጣቱን ወይም መሸሻሉን በመመርመር ላይ አነጣጥሯል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላትና ፅንሰ ሀሳቦች ብያኔ

- **አንብቦ መረዳት** (Reading Comprehension)፡-Chair(2002) አንድን ፅሁፍ በማንበብ መልዕክቱን በንቃት ለመረዳትና ጠቃሚ መረጃዎችን ለመለየት እንዲሁም በፅሁፉ ውስጥ አንድን ነገር መርጠን በማውጣት ትርጉም መስጠት እንደሆነ ሲያስረዱ Grellet (1991) ደግሞ አንብቦ መረዳት በአንባቢውና በፅሃፊው መካከል የሚደረግ መስተጋብር ስለሆነ በሁለት መንገድ ከፍሎ ማየት እንደሚቻልና ይኸውም የመጀመሪያው በምንባቡ ውስጥ በግልፅ የሰፈሩ ጉዳዮችን መረዳት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ተጠየቃዊ ዕውቀትንና ግምትን በመጠቀም በፅሁፉ ውስጥ በግልፅ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን አንብቦ መረዳት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡
- **አዕምሯዊ ብልሃት** (Cognitive strategy):-የሰው ልጅ አንድን ነገር እንዴት እንደሚረዳ፣እንደሚያስታውስ፣እንደሚያውቅና አዕምሯዊ ምስል እንዴት እንደሚከስት የሚያመላክት አዕምሯዊ የሆነንና አንድን የታሰበ አዕምሯዊ ሀሳብም ከግብ ለማድረስ የሚደረግ አዕምሯዊ የሀሳብ መመላለስ ነው፡፡ባጠቃላይ አንድን ነገር ለመስራት አዕምሯችን የሚያደራጀው የአሰራር ሂደት ወይም ንድፍ ማለት ነው(Marley et al. 2010፣ O' Mally & Chamot 1990 እና Oxford 1990)::
- **የመማር ብልሃቶች** (learning strategies)፡-አንድን ሀሳብ ለመረዳት መረጃ ለማከማቸት አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘት መማርን ለመቆጣጠርና ለመገምገም ወይም አንድን የተወሰነ ተግባር ለማከናዎን የሚጠቅሙ የተለዩ አስተሳሰቦች ወይም ስልቶች ናቸው፡፡የመማር ብልሃቶች በመማር ሂደት ውስጥ የጊዜ ትውስታንና የችሎታ ውስንነትን ለማሻሻል ማለትም መረጃን ካጭር ጊዜ ወደ ረዥም የጊዜ ትውስታ አሸጋግሮ ለመጠቀም በጣም አስፈላጊ ናቸው (O'mally & Chamot 1990; Pressley 2007)::

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ፅንሰሀሳብ ቅኝቶች

አንብቦ መረዳት ከፅሁፍ ቋንቋ ጋር መስተጋብር በመፍጠር በአእምሮ ውስጥ በአንድ ጊዜ ትርጉምን ፈልጎ ማውጣት እና መልሶ መገንባት ነው (Reading Study Group /RAND/ 2002)፡፡ ይህን ለማከናወን አንባቢ፣ ውሀድአሀድ፣ የማንበብ አላማ (ግብ) እና የማንበብ ብልሃት መስተጋብር ይፈጥራሉ፡፡ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማንበብ እና አንብቦ ለመረዳት ምን ማድረግ ያስፈልጋል የሚለው ጥያቄያዊ ሀሳብ የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ቁልፍ ጉዳይ ወይም ዋነኛ ትኩረት ነው፡፡ ይህ ምዕራፍም ጥናቱ የተነሳበትን አላማ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ ትኩረት የተደረገባቸውን ንድፈሀሳባዊ እና ተዛማጅ ፅሁፎች በዝርዝር አካቷል፡፡ ምዕራፉ በውስጡ የያዛቸው ዋና ዋና ንድፈሀሳባዊ ጉዳዮች አዕምሯዊ ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ፣ አዕምሯዊ የመማር ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለዉ ሚና ፣ማንበብን የመማር ብልሀቶችና አከፋፈል፣የአንብቦ መረዳት ምንነት ፣የማንበብ ደረጃዎች ፣ማንበብን የመማር ብልሀቶችን ማስተማሪያ ዘዴ፣የጥናቱ ንድፈሀሳባዊ ትውረት እና የቀደምት ጥናቶች ቅኝት የሚያመለክቱ ቅደም ተከተል ናቸው፡፡

## 2.2 አዕምሯዊ የመማር ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለዉ ሚና

ማንበብ ሰዎች ስላነበቡት ጽሁፍ ግንዛቤ የሚጨብጡበት ነው፡፡ የማንበብ ትምህርት የመጨረሻ ግቡም ይህ ነው፡፡ ግቡን ለማሳካትም ስለርእሰ ጉዳዩ የቀደመ እውቀትን መጠቀምም የተነበበውን መረጃ ትርጉም እንዲኖረው ማድረግ፤ ዋናው ዝርዝር ሃሳቦችን መለየትና ፍንጭ ጠቋሚዎችን መጠቀም የመሳሰሉት ተግባራትን ማከናወን ይገባል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ አንብበው መረዳት እንዲችሉ የቀረበውን ፅሁፍ በፍጥነት አቀላጥፈው ማንበብ ይኖርባቸዋል፡፡ በማለት አርምቡስራተር እና ሌሎች (2001) ገልጸዋል፡፡ ከዚህበላይ በቀረበው ጽሁፍ እንደምንረዳው የንባብ ክሂል ሲተገበር ለሰዎች በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ ትርጉም ያለው መረጃ ለሰዎች ሊያስተላልፉ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ማንበብ ፣ማንበብ አሁንም ማንበብ የማንበብ ብዛት የአቀላጥፎ ማንበብብ የመረዳት ደረጃ መሻሻልና ማደግ ይወስናል፡፡ ብዙ የሚያነቡ አንባቢዎች የማንበብ ክሂላቸው ስለሚዳብር ጥሩና አቀላጥፎ አንባቢዎች ሲሆኑ ጥቂት የሚያነቡ ደግሞ ለማንበብ የበለጠ የሚቸገሩ ይሆናል፡፡

(ሄራሽ (2000) እስኖች (2003) ጠቅሶ እንደገለፀው፡፡ ከቀረበው ገለጻ ለመረዳት እንደምንችለው ንባብን በመለማመድ ጊዜ ወይም ለንባብ ክሂል ትግበራ ሰፊ ጊዜ መሰጠት እንዳለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቶርማስንና ሁድሰን (2006) እንደገለጹት አንድን ፅሁፍ ድምፃችንን እያሰማን በምናነብበት ጊዜ ንግግር አስመስለን የምናቀርብበት ሂደት ነው፡፡ በዚህም አንባቢያን በጽሁፍ ውስጥ ያሉትን ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች በሚነበቡት መንገድ ማንበብ ይኖርባቸዋል፡፡ የድምጹ መጠን፣ቃና፣ ቅላጼ፣ ድምጸትና ወዘተ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ተጠቅመን መግለፅ አለብን፡፡ አንድን ጽሁፍ ስናነብ የንግግር አካል አድርገን ማቅረብ መቻል በጥሩ አገላለፅ ከማንበብ በተጨማሪ አንብቦ መረዳትንም ያመለክታል፡፡

ምንባብበሚነበብበት ጊዜ ልክ እንደ ንግግር አስመስሎ ማቅረብና የንባብ ክሂልን ለመተግበር ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ በጥሩ አገላለጽ  ማንበብ ተገቢ ነው፡፡ በጎኡኽና ቱንመር (1986) እንደተገለጸው መምህራን ማንበብን ለማስተማርና ክሂሉን ለማዳበር የዳበረ ቃላዊ ቋንቋን ለማስተማሪያነት መጠቀም አለባቸው የማንበብ ትምህርትን ለማጠናከር ከሚያስችሉ የቃላዊቋንቋ እውቀት ክፍሎች ውስጥ አንዱና በጣም ጠቃሚው የቃላት እወቀት ነው ህፃናት  በቃል ያዳበሩት የቃላት እውቀት የመረዳት፣ የመናገርና፣ የማንበብ፣ ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያስችል ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ህፃናት የቃላት እውቀት የሚያዳብሩት በመጀመሪያ ቃሉ ሲነገር  በመስማት ከዚያም የሰሙትን ቃል መልሰው ለሌሎች በመናገር ነው፡፡ ይህ በቃላዊ ቋንቋ ስለንግግር  ድምጾች የዳበረ ቃላትን የመማር ልምድ ህጻናት ትምህርት ቤት  ገብተው ሲማሩም የቃላት እውቀት ለማዳበርና ማንበብና መጻፍን ለመማር የሚያደርጉት ጥረት ማንበብን ይደግፍላቸዋል ፡፡ በተጨማሪም በቃላዊ ቋንቋ የዳበረ የስነ-ልሳን እውቀት፣ የተለመዱ የጽሁፍ ቋንቋ፣ የአረፍተ ነገር መዋቅሮችና የቃላት ክፍሎችን ለመማርም ያግዛቸዋል ይላሉ፡፡ ከገለጻው እንደምንገነዘበው የህጻናትን የቋንቋ እውቀት ለማበልፀግ መምህራን ያላቸው የቃላት ክምችት ወሳኝመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ልዩ ልዩ ንባቦችን እያነበቡ በመጡ ቁጥር ሰፊ የሆነ የቃላት እውቀት ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የንባብ ክሂላቸውን ለማበልጸግ ይችሉ ዘንድ አስቀድመው ያነበቡትን ምንባብ ለሌሎች በመንገር ክሂሉን መተግበር ሌላኛው መንገድ ነው፡፡

Hutunen (1996) እንዳሉት የቋንቋን ትምህርት ለተማሪዎች ከተለመደው አስራር ወጣ ተብሎ ብልሀቶችን በማሰልጠን ማስተማር ጠቀሜታው የጎላ ሲሆን እንደሚችልና በተለይም ክሂሎችን በማስተማር ዙሪያ ያላቸውን እዉቀት ለማጎልበት ያስችላል፡፡

Rubin (1987) እንዳሉት የቋንቋን መማር ብልሀቶችለተማሪዎች ማሰልጠንና ማስተማር በቋንቋ ውስጥ ያሉ አስቸጋሪ የሚባሉ ተግባራትን ለማከናወን ያስችላል፡፡ ውጤታማ የአነባበብ ዘዴዎች ለውጤታማ ንባብ የሚያግዙ ዘዴዎች ቅደም ተከተል ሲኖሩ እነሱም መፅሃፍትን መምረጥ፣መፅሃፍትን ከገዛን በኋላ ጓጉቶ ንባብ አለመጀመር፣አቅም የፈቀደውን ያክል የንባብ አካባቢን የተመቻቸ ማድረግ፤አእምሮን በማረጋጋት ራስን ዘና አድርጎ ከውጥረት ነፃ በመሆን ማንበብ፣መፅሃፉን ገልጦ ማንበብ ብቻ ሳይሆን ራስን የትረካውን ተሳታፊ በማድረግ በማንበብ ውስጥ መመሰጥ፣ከሚነበበው ፅሑፍ አንዳችም ቁም ነገር አገኛለሁ ብሎ መወሰን፤ አስፈላጊ ከሆነ በግል ማስታወሻ ደብተር ላይ ጠቃሚ ነጥቦችን መመዝገብ፤እና ከንባብ በኋላ መፅሃፉን ካነበቡ ሌሎች ሰዎች ጋር በመፅሃፉ ቅርፅና ይዘት ላይ መወያየት(Rubin 1987)፡፡

## 2.3 ማንበብን የመማር ብልሀቶችና አከፋፈል

ቋንቋን የመማር ብልሀት በ1966 Aaron Carton በሚባሉ ምሁር ‹‹The Method of Inference in Foreign Language Study›› በሚል ርእስ እንደ ተጀመረ Wenden & Rubin (1987) የሚገልጹ ቢሆንም በጥናት እና ምርምር ለመጀመርያ ጊዜ ቋንቋን የመማር ብልሀትን እና መነሳሳትን የፈጠሩት ግን Rubin (1975) እና Stern (1975) እንደሆኑ McDanough (1999) እና Griffiths (2004) ያስረዳሉ፡፡

የማንበብ ብልሀቶች አንባቢዎች አንድን ሥራ እንዴት እንደሚረዱ፣ ምን ዓይነት ጽሁፎችን እንደ ሚያነቡና እንዴት እንደ ሚያነቡ ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ አስቸጋሪ የሆነውን ክፍል እንደገና ማንበብ፣ የማይታወቁ ቃላትን ከጽሁፈ አውድ መረት፣ የአነበቡትን ጽሁፍ ማጠቃለል እና የአንባቢውን የቀደመ እውቀት ማወቅ ወዘተ. እንደሚያስፈልግ Carrell et al. (1989) ያስረዳናል፡፡ ማንበብን የመማር ብልሀቶች ተማሪው የራሱን እውቀት እና የንባብ ክሂል ከፍ ለማድረግ የሚጠቀምባቸው ብልሀቶች ናቸው፡፡ ለንባብ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንደ ብልሀት ነው፡፡ ምክንያቱም በንቃት ላይ የተመሠረተ ራስመር ተሳትፎ /self directed involvement/ ለማድረግ የመማር ብልሀት አስፈጊ መሣሪያ በመሆኑ የግንኙነት ብቃትን ለማበር መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ ተገቢ የሆነ ማንበብን የመማር ብልሀት መማር ከፍ ያለ በራስ መተማመንን ለመፍጠር ያስችል (Oxford 1990)፡፡

Richards & Lockhart (1996) እና Chamot (2004) እንደሚሉት ደግሞ ቋንቋን የመማር ብልሀቶች ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በተለያየ አቅጣጫ በማየት በራሳቸው ምርጫ እና በሚቀላቸው መንገድ እንዲማሩ እገዛ የሚያደርጉ መንገዶች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ Wenden & Rubin (1987) እና Mahdaui & Mehrabi (2013) ማንበብን የመማር ብልሀት ተማሪዎች የራሳቸውን ሀይል ተጠቅመው ቋንቋውን በሚማሩበት ጊዜ ውጤታማ ለመሆን የሚረዱ ልዩ ልዩ መንገዶችን ለመከተል ያለውን ብቃት የሚመለከቱ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጉዩን ስያሜ በተመለከተ የተለያዩ አጠቃቀሞች እንዳሉ Griffiths (2004) ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ፤ Oxford (1990) ቋንቋን የመማር ብልሀቶች፣ O'Malley and Chamot (1995) የመማር ብልሀት እንዲሁም Wenden & Rubin (1987) ደግሞ የተማሪው ብልሀቶች በማለት ሰይመዋቸዋል፡፡

ከላይ የተገለጹት ምሁራን ቋንቋን የመማር ብልሀቶችን በተለያየ መንገድ ከፍለው ያዩ ሲሆን፣ Oxford (1990)፣ Oxford (2003)፣ Mahdaui & Mehrabi (2013)፣ McDonough (1999)፣ Tudor (1996)፣ Richards & Lockhart (1996)፣ Griffiths (2004) እና Brown (1994) ደግሞ ቋንቋን የመማር ብልሀቶችን ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ ብልሀቶች በማለት በሁለት ዋና ዋና ክፍል ከፍለዋቸዋል፡፡ በቀጥተኛ ብልሀቶች ውስጥ የሚካተቱት የትውስታ ብልሀቶች (Memory Strategies)፣ አእምሮአዊ ብልሀቶች (Cognitive Strategies) እና አካካሽ ብልሀቶች (Compensation Strategies) ሲሆኑ፣ ከታሚው ቋንቋ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ በኢቀጥተኛ ብልሀቶች ስር የሚካተቱት ደግሞ ቋንቋን በማቀድ፣ በመገምገም እና ጭንቀትን በመቆጣጠር መማርን የሚያግዝ ናቸው፡፡ እነዚህም፤ አእምሮአዊ ብልሀቶች (Meta Cognitive Strategies)፣ ስነልቦናዊ ብልሀቶች (Affective Strategies) እና ማህበራዊ ብልሀቶች (Social Strategies) በመባል በሶስት ይከፈሉ፡፡

### 2.3.1 አእምሮአዊ የማንበብ ብልሀት

አእምሮአዊ ብልሀት ማለት የሰው ልጅ እንዴት ነው የሚያስበው? የሚረዳው? የሚያስታውሰው? የሚያውቀው? እና አእምሮአዊ ምስል የሚከስተው? የሚለውንየሚያመለክት ሲሆን፣ ከዚህም ሌሌ ትምህርት ላይ ትኩረት በማድረግ ሰዎች እንዴት እንደሚረዱ እና የውጭውን አለም ከራሳቸው ህይወት ጋር እንዴት እንደሚያመለክቱ

Collier & Hoover (1987) ፣ Marley et al. (2010) እና Lutz & Huitt (2004) ያስረዳሉ፡፡

አእምሮአዊ ብልሀት ተማሪዎች ውስብስብ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችላቸውን ውስጣዊ ሂደቶች ያዳብራል (Rosenshine 1997)፡፡ የማንበብ ግንዛቤ ለአእምሮአዊ የማንበብ ብልሀት አስፈላጊ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ራስን የመጠየቅ ብልሀቶችን ስንመለከት ተማሪዎቹ ምን እንዳነበቡ እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፡፡ Rosenshine (1997) እንደሚያስረዱትም፣ ጥያቄዎችን መፍጠር ወይም ማዘጋጀት በቀጥታ ወደ መረዳትአይመራም፡፡ ይሁንእንጂ ጥያቄዎች ሲነሱ ተማሪዎች ጽሁፊን ይመረምሩ እና መረጃ ይሰበስባሉ፤ ከዚያም ምን እንዳነበቡ ይረዳሉ፡፡ አእምሮአዊ የመማር ብልሀት ግብ የተማሪዎችን የትግበራ ዘዴዎች የመቆጣጠር፣የመጠቀም እና የመማር አቅም ማሳደግ ነው፡፡ ይህንን የትግበራ ዘዴ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በምናስተምርበትም ወቅት ማስታወስ ያለብን ነገር ስለ ትግበራ ዘዴው ለመዳ እና ቁጥጥር መማር ወይም መታወቅ እንዳለበት ነው (Collier & Hoover 1987)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አእምሮአዊ ብልሀት በግንዛቤያዊ ደረጃ ያለ እና ላጭር ጊዜ በሚቆየው አስታዋሽ የአእምሮ ክፍል (Short term Memory) አማካኝነት አእምሮአዊ ክንውን የሚካሄድበት ሲሆን፣ ቅጽበታዊ በሆነ መንገድ የማይገለገሉበት፣ ተማሪዎቹ ወደፊት በቋንቋ ትምህርት ሂደት ሉያገኙ በሚችሉት አዲስ ጽንሰ ሀሳብ ላይ የተለያዩ ተግባራትን በመፈጸም በትምህርት ሂደቱ ላይ መነሳሳት እንዲያሳዩ የሚያደርግ እንደሆነ O'Malley and Chamot (1995) ያስረዳሉ፡፡

አእምሮአዊ ብልሀት በመጠቀም ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ተግባራት እንዲቀርቡ ማድረግና ውጤታማነታቸውን (efficiency) መጨመር ይቻላል፡፡ ይህም የትምህርትን ተግባራት ማስታወስ፣ ከትምህርት ይዘቱ መረጃዎችን ተግባራዊ ማድራግ፣ ዓረፍተ ነገሮችንና አንቀጾችን ማዋቀር፣ የተጻፈ ስራዎችን አርትኦት ማድረግ፣ አንድን ሀሳብ በራስ አሳጥሮ መውሰድ እና ሉያስተምር በሚችል መንገድ መረጃዎችን መከፋፈልን ሉያካትት ይችላል ሆኖም ግን በዚህ ብቻ አይወሰኑም፡፡ እንደ Rosenshine (1997) አገላለጽ፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ አእምሮአዊ ብልሀት ስንጠቀም መምህሩ በተማሪዎች እና በሚማሩት ይዘት ወይም ክሂል መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት ድልድይ በመሆን ወሳኝ ሚና ይፈጽማል፡፡ ይህ ሚናም ተግባራቱ ማለቃቸውን መረዳትንና እንዲሁም የተግባራቱን አቀራረብ የሚመለከት ሲሆን፣ የተግባራቶቹ አቀራረብም እውቀትን የሚጠይቅ በመሆኑ ከተማሪዎች ጋር መነጋገርን እንደሚጠይቅ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም ሌላ ይህ ብልሀት ተማሪዎቹ አእምሮቸውን በመጠቀም ቋንቋን ለመማር የሚያግዙ ቁሳቁሶች፣ አጠቃላይ ሁኔታዎች፣ ሀሳባዊ ወይም ነባራዊ እና ተጨባጭ በሆነ መልኩ የሚገለገሉባቸው ብልሀቶች እንደሆኑ Oxford (1990) እና O'Malley and Chamot

(1995) ሲገልጹ በተመሳሳይ Salovaara (2005) ደግሞ አእምሮአዊ ብልሀት አእምሮአዊ ድርጊትን የሚያመለክት ሲሆን፣ እነዚህም የተለያዩ የትምህርት ግብን ለማግኘት ወይም የትምህርት ተግባራትን በራስ ለመስራት የሚያስችሉን እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡

### 2.3.1.1 አእምሮአዊ ንኡሳን ብልሀቶች

አእምሮአዊ የማንበብ ብልሀት አንደ የቋንቋ መማር ብልሀት እንደ ሆነ፤ ተማሪዎቹም ይህን ብልሀት ተግባራዊ ቢያደ ርጉ በትምህርታቸው የበለጠ ውጤታማ እንደ ሚሆኑ እና እንዲሁም በዚህ ብልሀት ስር የተለያዩ ንኡሳን ብልሀቶች እንደ ሚካተቱ Oxford (1990)፣ O'Malley & Chamot (1995)፣ Salovaara (2005)፣ Ratna (2014) እና Ozek & Civelek (2006) ያስረሉ፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የተለያዩ የአእምሮአዊ ብልሀት አይነቶችን በንባብ ትምህርት ክፍል ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ አንብቦ የመረት ችልታን እንዴት ማበር እንደ ሚቻል ሙከራዊ ጥናት በማድረግ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፡፡ በአጠቃይ ቋንቋን በመማር ብልሀት አከፋፈል ውስጥ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው እነዚህ ብልሀቶች የቋንቋ መማር ብልሀቶች በመሆናቸው አራቱንም የቋንቋ ክሂልች ለማስተማር ያገለግሉ፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት በንባብ ጊዜ ተግባራዊ የሚሆኑት ይ በማተኮሩ ከአሉት አእምሮአዊ የመማር ብልሀት መካከል አንብቦ መረትን ለመስተማር የሚሆኑትን ብቻ በመምረጥ በዚህ ጥናት ለማካተት ተሞክሯል፡፡ እነዚህም ፡- የመደ ጋገም፣ ቁልፍ ቃትን የመጠቀም፣ ምስል የመከሰት፣ ሀሳብን በፍጥነት የማግኘት፣ አውድ የመጠቀም፣ ማስታወሻ የመያዜ፣ ምንጭ የመጠቀም፣ የመተርጎም እና የማጠቃለል ብልሀት ናቸው፡፡

### 2.3.1.2. አእምሮአዊ የማንበብ አስተሳሰቦች

የተለያዩ የንባብ ንድፈ ሀሳቦች አንብቦ በመረት ውስጥ ያለውን ሂደ ት በተለያየ መንገድ ለመግለጥ ሞክረዋል፡፡ ስኬታማ የንባብ ልምድ እንዴት ሊመጣ እንደ ሚችል ወይም አንብቦ በመረት ሂደ ት ውስጥ ሊያጋጥም የሚችልን ችግር ለመመልከት ሞክረዋል፡፡ አእምሮአዊ የማንበብ ንድፈ ሀሳቦች ንባብን የሚመለከቱት ፍጹም አእምሮአዊ ሂደ ት አድርገው ነው፡፡ አስቀ ድሞ በ1980ዎቹ ንባብ ሌልች ውጫዊ እንቅስቃሴዎችን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ማህበራዊ እንቅስቃሴ ተኮር ተደ ርጎ ይታይ ነበር፡፡ የስነሰብ ሉቃውንት (humanist) ዘመን እየተባለ በሚጠራው ዘመን ማለትም በ1990ዎቹ ደ ግሞ ንባብ ስሜታዊ ትውረት (affective theories) ውስጥ የሚታይ ነበር፡፡ ነገር ግን በቅርቡ በልእለ አእምሮአዊነት እና አዲስ የትምህርት ጥናቶች ውስጥ እንደ ተመለከተው ብልሀቶችንና ማኅበረ-ባህዊ (sociocultural) ልምዶችን እንደ ሚወስድ ከግንዛቤ ይ ተደ ርሷል (Boakye 2012 )፡፡

ንባብ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአብዛኛው አእምሮአዊ እንቅስቃሴ ተደ ርጎ ይቆጠራል። በዚህ ዘመን የአእምሮአዊያን እና የባህራዊያን ትውረት በንባብ ንድፈሀሳቦች ይ እና ንባብን በማስተማር ይ ተጽእኖ መፍጠር ችለዋል። በመሆኑም በዚህ ዘመን ንባብን በማስተማር ዙርያ ተጽእኖ መጠር የቻሉ ንድፈሀሳቦች ከታች ላይ (bottom- up) እና ላይ ታች (top-down) ንባብን የማስተማሪያ ሞዴልን ይጠቀሙ ነበር (Alexander & Fox 2008፤ Aldreson 2000፤ Grabe & Stoller 2002 እና McLaughlin 2008 )። እንዲሁም Davies (1995)፣ Nuttall (1996)፣ Aebersold & Field (1997) እና Carrell (1998) ንባብን ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ሞዴሎች የተለያዩ ቢሆኑም ከሚከተሉት የትኩረት አቅጣጫ አንጻር በሶስት ዋና ዋና ክልች ከለዋቸዋል። እነዚህም፣ ታችይ (Bottom-up)፣ ይ-ታች (Top-down) እና መስተጋብራዊ (Interactive)ሲሆኑ፣ ይህ ጥናትም እነዚህን ሶስት ሞዴልች በዜርዜር ለማየት ሞክሯል።

## 2.4 የአንብቦ መረዳት ምንነት

ማንበብ ማለት ምን እንደሆነ ሲገለጽ Bachman (1990) ንባብ ማለት መረዳት፣መተርጎም፣ መፍታት፣ በስሜት መድረስ፣ መቀበል፣ መገንዘብ፣ መለየት፣ መነጠልና መቁጠር ነው ይላል።

ድምጽ ማውጣት መናገር ንበት ነው ይላል። አንድን ፅሑፍ ለማንበብ ከመወሰናችን አስቀድሞ የምናነባቸውን የፅሑፍ አይነቶች ለይተን መወሰን ይኖርብናል። የዘርፉ ጠበብቶች ከመጽሐፍት ንባብ የሚገኑ የዕውቀት አይነቶችን የሚመድቧቸው በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ነው።የመጀመሪያ ዕውቀት ተግባራዊ ዕውቀት ይባላል። ከመጽሐፍት ንባብ የሚገኙይህን የዕውቀት አይነት ነገሮችን ለመፈበረክ፣ ወይም የተፈበረኩ ቁሳቁሶችን ለመፍታትናለመግጠም፣የመድሐኒት አጠቃቀም ዘዴ፣የምግብ አዘገጃጀት ዕውቀት፣ የመሳሰሉትን ዕውቀቶች በቃሉ ከንባብ ማግኘት ይችላል። ሁለተኛው ዕውቀት ለመረጃ የሚጠቅም የዕውቀት አይነትነው። የመረጃ ዕውቀት የሚያስጨብጡ መጽሐፍት ስህተትን ደግሞ ላለመፈጸም ወይም ነገሮችን፣ አካባቢንና ሁኔታን ቀድሞ ለማወቅ አውቆ ለመዘጋጀት ግንዛቤ ያስጨብጣሉ። ሶስተኛው ዕውቀት ለአጠቃላይ ግንዛቤ የሚረዳ የዕውቀት አይነት በመባል ይታወቃል። ይህንን መሰሉ ዕውቀት የሚገኘው በአብዛኛው ከመማሪያ መጽሐፍት ወይም ቀደም ሲል የተገኘን ዕውቀት ለማዳበር፣ግንዛቤን ለማስፋት፣ የተለያየ ግንዛቤ ለማግኘት የሚፈለግ ሰው ከሚያገኛቸው መፃህፍት ውስጥ የሚገኝ የዕውቀት አይነት ነው።አራተኛው ዕውቀት ተምኔታዊ ቢባል ያስኬዳል። ተምኔታዊ ዕውቀት መልካምታሪክ

ከሆነ ተደስተን መጥፎውን ደግሞ ተፀይፈን የምንገነዘበው፣ የምንገረምበትና ምንደመድምበት የዕውቀት አይነት ነው (clece-Murcia 1991)::

## 2.5 የማንበብ ደረጃዎች

የመጀመሪያ ደረጃ ከማንበብ በፊት(ቅደመ-ንባብ) የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስና የምንባቡን ሃሳብ መገመት(መተንበይ) ሲሆን ሁለተኛው ንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚጠቅምና ሶስተኛው ድህረ ንባብ ሆኖ ይህም አንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ አመራማሪና ከምንባቡ የወጡ ሆነው ተዘጋጅተዋል።

### 2.5.1 የብልሃት ምንነት

ብልሀት የምንለው አንድን ተግባር (ስራ) ወይም አስቸጋሪ ሁኔታን ባግባቡ ለማሸነፍ የሚደረግ ስልታዊ አሰራር ነዉ። ታዲያ በትምህርት አሰጣጥሂደትምይህን ተግባር ለተማሪዎች ተግባራዊ ቢደረግ ተማሩትን ትምህርት ከመደበኛው ማስተማር ሂደት የተለየ ትኩረት ሰጥተዉ በነቃ አዕምሮ ሊከውኑትና ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ግለሰቦች አንድን ሀሳብ ለመረዳት፤መረጃ ለማከማቸት፤ አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘት፤መማርን ለመቆጣጠርና ለመገምገም፤ወይንም አንድን የተወሰነ ተግባር ለማከናዎን ሂደት ውስጥ የአጭር ጊዜ የትውስታ ችሎታ ውስንነትን ለማሻሻልና ትውስታንም ከአጭር ጊዜ ወደ ረዥም ጊዜ አሸጋግሮ በመጠቀም በጣም አስፈላጊዎች መሆናቸውን (O'mally &chamot 1990):: ይገልጻሉ።

ቋንቋንየመማር ብልሃቶች የቋንቋን ተግባራት ለማሳካት የሚተገበር ሲሆን ተማሪዎች ካላቸውዕውቀት ላይ ብልሃቶችን ተግባራዊ በማድረግና በመጠቀም በቋንቋ ትምህርቶች ውስጥ የሚተገበሩትን ክሂሎችና ዕውቀቶች ከፍ ለማድረግ የሚጠቀሟቸው ብልሃቶች ናቸው።በተግባራት ውስጥም ትምህርቱን በንቃት እየተከታተሉ ራሳቸውን መገምገምና መቆጣጠር፤ድክመቶቻቸውን በማጠናከር የሚያግዙ ብልሃቶች ናቸው (oxford1990 እና Hsiao and oxford 2002):፡ የቋንቋመማር ብልሀቶች የቃላትን ፤ ንባብን ፤ስዋስዉን ፤ማዳመጥን፤ መናገርንና የመፃፍ ትምህርትለማጎልበት የሚረዱ የተማሪዎች ልዩ የመማር መንገዶች ናቸው (Schmitt, 1997; omalley&chamot, 1990)፡፡

Oxford (2003); nation (2001) እና schmit (1997) እንዳስገነዘቡት የቋንቋን መማር ብልሀቶች ሂደት አዳዲስ ነ ገሮችን ለመርዳትና ለርዥም ጊዜ ትውስታን መዝግቦ ለማቆየትና ራሳቸውን ለመርዳት የሚጠቀሙባቸው ተለያዩ ስልቶች ናቸው ለተማሪዎች ብልሀቶችን ማሰልጠንና በአግባቡ ከተተገበሩ የተማሪዎችን ብልሀት እውቀት ብቻ

ሳይሆን የሚያዳብሩት ተነሳሽነታቸውና አጠቃቀማቸውን ጭምር ይሆናል: rubin እና ሌሎች (2007)

Rubin (1987) እንዳሉት አምሮአዊ ብልሀቶች ተማሪዎች ተተኳሪውን ቋንቋ ሲማሩ በቀጥታአምሮአቸውን በመጠቀም የሚተገብሩአቸው የአስራር መንገዶችን የሚወስዱአቸው ረምጃዎች ወይም ችግርማቅለያዎች ናቸው።

## 2.6 ማንበብን የመማር ብልሀቶችን ማስተማሪያ ዘዴ

Oxford (1989) እና Kouarogo (1993) እንደ ሚገልጹት፣ በቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ ለሆኑትም ሆነ ውጤታማ ልሆኑት ተማሪዎች ቋንቋን የመማር ብልሀቶችን ማሰልጠን ማለት ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርታቸው ሂደ ት ምን? እንዴት? መቼ? እና የት? መማር እንለባቸው የሚያግዝ አማራጭ መንገዶችን ማመከት ማለት ነው። የብልሀት ትምህርት አሰጣጥ በሁለት መልክ እንደ ሚሰጥ ምሁራን ይገልጻሉ። O'Malley & Chamot (1995) ስለእነዚህ የትምህርት አሰጣጥ ልዩነት ሲገልጹ፣ አንደ ኛ የብልሀቶቹ የትምህርት አሰጣጥ ብልሀቶችን ከሌ ትምህርት በመነጠል ለብቻ የማስተማር አቀራረብ ሲሆን፣ ሁለተኛ ብልሀቶችን ከክል ትምህርት ጋር አቀናጅቶ የማስተማር አቀራረብ ነው። ‹ ስለሆነም ሁለቱ የብልሀት ትምህርት አቀራረቦች የየራሳቸው ጠንካራ እና ደ ካማ ጎን ቢኖራቸውም ከክል ትምህርት ጋር ተቀናጅቶ የሚቀርበው ለመምህራን አነስተኛ ስልጠና በመስጠት ተግባራዊ ሉደ ረግ የሚችል በመሆኑ ጠቀሜታ አለው (O'Malley and Chamot 1995)። ተማሪዎች በጥናት ከተደ ራጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እና ትምህርታዊ ክንውኖች (Activites) ተነስተው የብልሀቶችን ጠቀሜታ መረት እንደ ሚችሉ O'Malley and Chamot (1995) ያስረሉ። ከዚህም ሌላ McCormick et al. (1989) ብልሀቶችን ለብቻ ነጥል ከማስተማር ይልቅ ከተለያዩ የትምህርት አይነቶች ለምሳሌ ከንባብ፣ ከመጻ ክሂል ወዘተ. ጋር አቀናጅተን በማስተማር ማለማመድ ተማሪዎቹ በብልሀቶቹ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንደ ሚያበረታታ ያስረሉ። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚመርጠው ብልሀቶችን ከክል ትምህርት ጋር አቀናጅቶ ማስተማርን ስለሆነ ከንባብ ክሂል ትምህርት ጋር አቀናጅቶ በማስተማር ጥናቱን ለማካሄድ ተሞክሯል። ከዚህ አኳያ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ከተለያዩ የማንበብ ብልሀት ዓይነቶች ጋር ሉያስተዋውቁ የሚችሉ የተለያዩ ምንባባትን እና የተለያዩ የአንብቦ መረት ጥያቄዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። Ur (1996) ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ተማሪዎችን ወደ ተለያየ

በአጠቃይ የትምህርታዊ ተግባራት እውቀት ማለት ትምህርታዊ ተግባራትን ግብ መቺ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚያስፈልጉ ቅድመ ተከተልችን ማወቅ ሲሆን ተማሪዎችን ከተለያዩ

የንባብ ብልሀት አይነቶች ጋር ለማስተዋወቅ መምህራን የመማሪያ መጻሕፍቱን በማየት የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራት ማዘጋጀት እና ተማሪዎችን ማለማመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 2.6.1 ማንበብን የመማር ብልሀት ማሰልጠኛ ሞዴል

ተማሪዎች የተለያዩ የቋንቋ ተግባራትን በሚሰሩ ጊዜ የመማር ብልሀቶችን እንዴት አድርገው መጠቀም እንለባቸው እንዲሁም ሌልች አዲስ ተግባራትንና ይዘቶችን በመማርያ ክ ውስጥም ሆነ ከማማርያ ክ ውጭ ተግባራዊ በሚያደ ርጉበት ወቅት ብሀቶችን እንዴት መጠቀምና ማስፌፌት እንለባቸው በማስተማር መምህራን ታቅ ሚና መጫወት እንለባቸው Chamot and O'Malley (1994) ያስረሉ፡፡ ስለሆነም የብሀት ስጠናን ለማሳደ ግ ተመራማሪዎች በተለያዩ ሞዴልች ይ ምርምር እና ሙከራ አድርገዋ፡፡ በመሆኑም አጥኝዋ ባደ ረገችው አሰሳ የ Pearson and Dole (1987)፣ የOxford (1990) እና የChamot (2005) ሞዴ የተመለከተች ሲሆን፣ የሶስቱንም ምሁራን ሀሳብ ከዚህ በታች ለማየት ተሞክሯ፡፡ የ Pearson and Dole (1987) ሞዴ ስንመለከት ለመጀመርያ ቋንቋ ተማሪዎች ስጠና መስጫ የተነደ ፈ ሲሆን ይህ ሞዴ አጥብቆ የሚመክረው መምህራን መጀመርያ ለተማሪዎቹ የተወሰኑ ብሀቶችን እና ሞዴልችን ተግባራዊ ማድረጋቸው ጠቀሜታ እንለው ለተማሪዎቹ ማብራራት፤ እንዲሁም ተማሪዎቹ ሲከታተሎቸው የነበሩ

ብሀቶችን ወደ  አዲስ አካባቢ ማስተለ እንለባቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ብሀቶቹ መጀመርያ በመምህሩ ሞዴ ከሆኑና ተማሪዎቹ በግ ከተለማመዶቸው የተለያዩ ብሀቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የተሻለ ተረድኦት ሉኖራቸው እንደ ሚች ያስረሉ፡፡

በመጨረሻም የ Chamot (2005) ሞዴ ስንመለከት ይህ ሞዴ ‹‹Cognitive Academic Language Learning Approach (CALLA)›› የሚለውን የንባብ ዘዴ መሰረት ያደ ረገ ሲሆን፣ በ O'Malley እና Chamot የተጠና ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተማሪዎች ገጭ የሆነ እውቀትን እንዲይዝ እንዲሁም ራሳቸውን ወደ  ፌጣን አንባቢነት እንዲቀይሩ የሚያስች ዘዴ ነው፡፡ ይህ ጥናትም ከአእምሮአዊና እለአእምሮአዊ ጋር የተያያዘ የንባብ ብሃቶችን የሚያይ ሲሆን መሠረቱን ያደ ረገው አእምሮአዊ የመማር ንድፈሀሳብ (cognitive learning theory) ይ ነው፡፡ እርሱም ገጭ የሆነ እውቀት ወደ  ቅደ ም

ተከተዊ ወደ ሆነው እውቀት የመጓዜ ሂደ ት ሲሆን በመማር ብሃት /starategy instruction/ አማካኝነት የሚፈጸም ነው፡፡

### 2.6.2. ጾታና ማንበብን የመማር ብሀቶች

ምንም እንኳን አንንድ ጥናቶች ወንዶችና ሴቶችን ማንበብን በማስተማር ረገድ የተለያዩ ማንበብን የመማር ብሀቶች እንሉ ቢናገሩም ሌልች ግን በሁለቱ መካከ ዩነት እንደ ሌለ አመክተዋ (Green and Oxford 1995፣ Wharton 2000):: አንንድ ጥናቶች ወንዶችና ሴቶችን በተመለከተ ንከተለው የሚገባውን ብሀት እንደ ሚከተለው አመክተዋ። Wharton (2000) ሲንጋፖር ውስጥ በሚገኝ አንድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በ677 ተማሪዎች ይ ባካሄደት ጥናት ወንዶች ከሴቶች ይቅ የተሻለ ብሀቶችን በተደ ጋጋሚ

እንደ ሚመለከቱ በጥናታቸው አረጋግጠዋ። በሌ ጥናት Oxford et al. (1993) በሌ መኩ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ የተሻለ ብሀቶችን እንደ ሚጠቀሙ ጽፈዋ። Dreyer and Oxford (1996) በ179 ሴቶችና 127 ወንዶች መካከል ደቡብ አሪካ ውስጥ ባደ ረጉት ጥናት እንደ ተመለከቱት ሴቶች ማኅበራዊና እለአእምሮአዊ ብሀቶችን ከወንዶች በተሻለ ተጠቅመው አግኝተዋቸዋ።

Peacock and Ho (2003) ቻይና ውስጥ ባደ ረጉት ጥናት ሁለተኛ ቋንቋን ከሚያጠኑ 1005 ተማሪዎች በወሰደት ናሙና እንደ ገለጹት ሴቶች ስድስቱንም ዓይነት የማንበብ ብሀቶች (በአጥኚዎቹ የተዘጋጁትን) ተጠቅመው ተገኝተዋ። ከዚህም በተጨማሪ Nisbet፣ Tindall and Arryo (2005) እንደ ሚሉት በሴቶችና በወንዶች መካከ በብሀት አጠቃቀም ይ የሚታየው ዩነት ከባህዊ መቼታቸው ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው። አስቀድመው ከነበሩት ጥናቶች በተቃራኒው አንንድ ጥናቶች በብሀት አጠቃቀም ይ በሴቶችና በወንዶች መካከ አንች ዩነት የለም በማለት ያስረሉ። Abu Shmais (2003) ባደ ረጉት ጥናት በወንዶች እና በሴቶች መካከ አንች ዓይነት ዩነት እንደ ሌለ ያስረሉ።

### 2.6.3 ማንበብን የመማር ብሀቶች አጠቃቀም ደረጃ

በተደጋጋሚ እንደ ተገለጠው በከተኛ ብቃት ደ ረጃ ይ የሚገኙ ተማሪዎች ብዙ ብልሀቶችን የሚጠቀሙ ከመሆናቸውም በይ በአግባቡ ይጠቀሙባቸዋ። ይህ ሁኔታ ንባቡን ለመረትና ለመገንዘብ አስፈጊ እንደ ሆነ Alderson (2000) ያስረሉ። በተቃራኒው ዜቅተኛ የሆነ ውጤትን ያመጡ አንባቢዎች ብሀቶችን እንዴት መጠቀም እንደ ሚገባቸው ያወቁ ናቸው። Zhang (2001) ያጠናው አንድ ጥናት እንደ ሚያመለክተው በንባብ ከተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ዜቅተኛ ውጤት ካቸው ይቅ የበለጠ ስለብሀቶች አጠቃቀም የተገነዘቡ ሆነው ተገኝተዋ። ‹‹ በሌ ጥናት Yin and Agnes (2001) እንደ ጠቆሙት፣ ጥሩ አንባብያን የበለጠ እለአእምሮአዊ ብሃቶችን የሚጠቀሙ ናቸው። ምክንያቱም ስለነዚህ ብሀቶች የበለጠ ግንዛቤያቸው ናቸውና። Phakiti (2003) እንደ ሚለው፣ ውጤታማ የሆኑ ቴስት ወሳጆች

ከአእምሮአዊ ብሀት ይቅ እለአእምሮአዊ የሆነውን ብሀት አዘወትረው የሚጠቀሙት እንደ ሆኑ ሲያስረደ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ Vandergrift (1999) ባደ ረጉት ጥናት እንደ ጠቆሙት ደ ግሞ ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች እአእምሮአዊ የሆነውን ብሀት በመጠቀም ረገድ የተዋጣቸው ናቸው፡፡ አስቀድመው ከተደ ረጉ ጥናቶች ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻለው የተዋጣቸው ተማሪዎች ከአእምሮአዊ ይቅ እለአእምሮአዊ የሆነውን የማንበብ ብሀት እንደ ሚጠቀሙ ነው፡፡

## 2.7 የጥናቱ ንድፈሀሳባዊ ትውረት

ጥናቱ በሁለት ንድፈ ሀሳቦች ይ ትኩረት ያደ ርጋ፡፡ እነዚህም፤ የ Piaget (1970) አእምሮአዊ ንድፈሀሳብ (cognitive theory) እና የ Bandura (1986) ማህበረ አእምሮአዊ ንድፈሀሳብ (social cognitive theory) ናቸው፡፡ አንብቦ መረት በአንባቢውና በሚነበበው ጽ መካከ የሚደ ረግ ሁለትዮሽ ግንኙነትን የያዘ ውስብስብ ሂደ ት ነው፡፡ በንባብ ሂደ ት እጅግ አስፈጊ የሆነው ግብ መረት ነው፡፡ አንብቦ መረት ተከናውኗ ብለን የምናስበው አንባቢው ከሚያነበው የንባብ መሳሪያ (ጽ) ትርጉም ሲያወጣና መመስረት ሲች ነው (Lipson and Wixson1986)፡፡ አእምሮአዊ ሂደ ትም መጀመሪያ የሚከሰተው በማህበራዊ ንድ (Social plane) ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሌልች ሰዎች ጋር በሚያደ ርጉት ግንኙነት ሲሆን፣ በኂ ይም ተማሪዎቹ ሁኔታዎችን የራሳቸው ስብእና በማድረግና ከሌልች የወሰደትን ወይም የተጋሩትን ዘዴ ወደ ግለሰብ ንድ በመለወጥ ይረደታ (Vygotsky 1962)፡፡ አእምሮአዊ ንድፈሀሳብ ትኩረት የሚሰጠው በሂደ ት በሰው ጅ አእምሮ ውስጥ ስለሚመጣው ነገር፣ የቋንቋ ለመ እና ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅር ነው፤ በዚህ ምክንያትም የመምህሩ ሚና መሆን ያለበት ተማሪው ካለው የተለያየ ምድ የትምህርት ውጤቱ ይ ተጽዕኖ ካመጡ ነገሮች በመነሳት ተማሪዎቹ ያሉበትን ደ ረጃ መረት፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳዩት ባህሪ ይ መወሰን እና አዲስ መረጃዎችን በማደ ራጀት የትኞቹ ውጤታማ እንደ ሆኑ መመርመር እንዲሁም ምጋቤ ምሾችን በመስጠት በቅደ ም ተከተ አዲስ መረጃዎችን ማዘጋጀት እና የበለጠ ውጤታማና ቀጣፊ

እንዲሆኑ ማድዬረግ እንደ ሆነ Wijayanti (2013)፣ Schunk (2012) እና Piaget (1970) ያስገነዘባሉ፡፡

ከዚህም ሌላ Piaget (1970) እና Chinn (2011) ስለ አእምሮአዊ ንድፈሀሳብ ሲገጹ፣ ሰዎች ሲያነቡ ከጽ ውስጥ ያገኙትን አዲስ እውቀት አጭሩ ትውስታቸው ውስጥ ከተመሳሳይ ራዊ እውቀታቸው ጋር እንዴት እንደ ሚያገናኙ፣ አጭሩ ትውስታቸው ውስጥ የገባውን አዲስ እውቀት ከራዊ እውቀታቸው በመነሳት እንዴት እንደ ሚረደት እና

የተረደትን አዲስ እውቀት ቋሚ እንዲሆን ረጅሙ ትውስታቸው ውስጥ ቀደ ም ሲ ከነበረው ተመሳሳይ ራዊ እውቀት ጋር እንዴት እንደ ሚያሰናስሉት የሚያሳይ እንደ ሆነ ያስረሉ። በተጨማሪ አእምሮአዊ ንድፈሀሳብ አንባቢው ሲያነብ አእምሮ ውስጥ ለሚያከናውናቸው ተግባራት ትኩረት የሚሰጥበት እንደ ሆነ ምሁራኑ አክለው ይገጻሉ።

አእምሮአዊ ንድፈሀሳብ በተማሪዎቹ አእምሮ ውስጥ የሚከሰተው አውቀውት ነው። ከዚህም በላይ ንድፈሀሳቡ ትኩረት የሚያደ ርገው ሰዎች እንዴት ያስባሉ? እንዴት ይረሉ? እና ሰዎች እንዴት ያውቃሉ? የሚለውን ነው። ሰዎች እንዴት ያስባሉ የሚለው እኛ የምናስብበት መንገድ እንዴት ባህሪያችን ላይ ተጽኖ እንደሚያሳድር ሲያመለክት፣ ሰዎች እንዴት ይረሉ? የሚለው ደ ግሞ የማህበረሰቡ ተረድኦት ከውጪው አለም ጋር ያለውን ግንኙነት ያሳያ። በመጨረሻም ሰዎች እንዴት ያውቃሉ? የሚለውን ስንመለከት በውጭው አለም ይ ያሉ ክስተቶችን እንዴት ያውቃሉ? የሚለውን ያሳያ። እነዚህ ነገሮች የመጡት በሂደ ት ቢሆንም የተከሰተው ግን በሰው ጅ አእምሮ ውስጥ ነው (Asiae university፣ 2012:107)።

በተጨማሪም አእምሮአዊ ንድፈሀሳብ የአእምሮ ሂደ ትን የሚያጠና ሲሆን፣ ስሜት፣ የጠለቀ አስተሳሰብ፣ ትኩረት፣ ማራጀት (encoding) እና ትውስታ ይ ጥናት ማድረግን ይጠይቃ። ስሜት (sensation) የሚያመለክተው መነቃቃት እንዴት ከውጫዊ ቀስቃሽ እንደ ሚመጣና ወደ ሚከተለው ሂደ ት ከመኩ በፉት እንዴት በ sensory (ስሜት) ውስጥ እንደ ተመዘገበ ሲያሳይ፣ የጠለቀ አስተሳሰብ (perception) ደ ግሞ እንድን ነገር በሂደ ት በማሳየት መተርጎም እና የመስማት ወይም የመረት ችሎታ ነው። የዚህ ሁኔታ መታወቅም፣ አማን ማወቅ፣ ታች ይ እና ይ ታች ሂደ ትን እና አንድን ነገር መረትን ያካትታ። ሶስተኛው ትኩረት ሲሆን፣ አንድን ነገር ለመስራት ትኩረት መስጠትን የሚመለከት ነው። ከሌልቹ ይቅ በጣም ጠቃሚ ነው እንዲሁም ስለምናውቀው ነገር ያለንን ግንዛቤ እንድናውቅ ይጠቅመና። አራተኛው ማደ ራጀት (encoding) ሲሆን፣ ትኩረት የሚያደ ርገው አስፈጊ የሆኑ መረጃዎችን ማደ ራጀት ይ ነው። የመጨረሻው ትውስታ (Memory) ሲሆን፣ ትውስታ በአእምሮአችን ውስጥ ያለውን መረጃ የማስታወስ እና የማቆየት ችሎታ ነው። ይህ በውስጡ የአጭር ጊዜ ትውስታ፣ የረጅም ጊዜ ትውስታ እና ስሜትን ያቀፈ ችሎታ ናቸው (Jordan, Carlite & Stack, 2008፣36)።

በመቀጠልም Davis (1995); Nutall (1996) እና Carrel (1998) ንባብን ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ሞዴሎች የተለያዩ ቢሆኑም ከራሳቸዉ የትኩረት አቅጣጫ በመነሳት በ3 ዋናዋና ክፍሎችመደበዉ አስቀምጠዋል። ይኸዉምታህታይ-ላዕላይ (Bottom-up)፤ ላዕላይ-

ታህታይ (TOP-down) እና መስተጋብራዊ (Interactive) ሲሆኑ በዚህ የጥናት ሂደትም ሦስቱንም የማንበብ ሂደት ሞዴሎች በቅደም ተከላቸዉ ተዘርዝረዋል፡፡

### 2.7.1 ታህታይ - ላዕላይ የማንበብ ሂደት ሞዴል

ይህየማንበብ ሂደት ሞዴል በ1950ዎቹ አካባቢ በባህሪያዊያን ሥነ-አዕምሯዊ ትዉረት ተጽዕኖ የፈጠረ የማንበብ ሂደት ሞዴል ነው ፡፡ በባህሪያዊያን ትውረታዊ አተያይ መማር የባህሪ መመስረት ሲሆን ድግግሞሽ፤ ማነቃቃት፤ እና ምላሽ መስጠት (የሚታይ ተግባር) ለቋንቋ መማር (መልመድ) ወሳኝ ተግባራት እንደሆኑ አስረድተዋል (Ertmer &Newby 2013; 48; Omaggion 1993; 45):: Kintsch (1988) አንብበቦ የመረዳት መዋቅራዊ ሞዴልን ካስተዋዎቁት ምሁራን ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡ በባህሪያዊያን አተያይ የማንበብ ሂደት ከእይታ መረጃ አንጻር ሲታይ አንድን ምንባብ አንብቦ ፊደልናቃላትን መለየት፤አንባቢን በማነቃቃትና ፍችን መልሶ በማዋቀር መገንዘብ ያስችላል የሚል ነው፡፡

በታህታይ- ላዕላይ የማንበብ ሂደት ሞዴል ዉስጥ የቀረበውን ጽሁፋዊ ምስል ለማንበብና ለመተርጎም ከመስመራዊ ዕድገት የሚጀምርና በሥነ-ትርጉም ውክልና የሚጨርስ ነው ይላሉ ምሁራኖች፡፡ Ling (2011: 9) ሞዴሉ ከመስመራዊ ሂደት እድገት የሚታይበት ሲሆን እድገቱም ከሥነ-ድምፃዊ ደረጃ እስከ ስነ-አገባብ በመቀጠልም ቀስ እያለ ወደ ሥነ-ትርጉም ደረጃ እያደገ የሚሄድ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ሞዴል አንባቢው ምንባቡን አንብቦ የትርጉም አሻሚነት ሊያጋጥመው በሚችልበት ጊዜ ያህንን ችግር ለመፍታት ወደ ሥነ-ድምፅና ሥነ-አገባብ ደረጃ መመለስ ሲችል ነው፡፡ የታህታይ-ላዕላይ የማንበብ ሂደት ሞዴል ዝቅተኛ የማንበብ ሂደት በመባል በምሁራኖች ትችት ቀርቦበታል Ling (2011; 9-10) እንደገለፁት ፡፡ እንዲህ እያለ ታህታይ-ላዕላይ ሞዴል ተቀባይነቱን እያጣ ሄደ፡፡ይኸውም የማንበብ ማንኛውም ሂደት ከፊደላት ጋር መስተጋብር በመፍጠር ይገኛል በሚል ብቸኛ ሀሳብ ላይ ትኩረቱን በማድረጉ ነው፡፡ የታህታይ-ላዕላይ የማንበብ ሂደት ሞዴል ከዚህ ትችት በኋላ በላዕላይ- ታህታይ ሞዴል ተተክቷል፡፡

### 2.7.2 የላዕላይ-ታህታይ የማንበብ ሂደት ሞዴል

Alexander & fox (2008): የላዕላይ- ታህታይ ሞዴል ሞዴል ላይ በተፈጠረው ክፍተት ምክንያት የተገኘ ሲሆን Muricia 1991): ይህ ሞዴል ፅንሰ ሃሳባዊ ተኮር ሞዴል በመባል በመባል ይታወቅ የነበረ ሲሆን፤ ሞዴሉየሚያንፀባርቀውም አንባቢውያለውን የቀደመ ዕዉቀት ወይም ልምዱን መሰረት በማድረግ ምንባቡን መገመት የሚችልበት ነው፡፡ Ling (2011: 9) በላዕላይ-ታህታይ ሞዴል ውስጥ አንባቢዎች የማንበብ ብልሃታቸውንና የማንበብ ክሂላቸውን በመጠቀም የደራሲዉን የሃሳብ ምንነትና ምን አይነት መልእክት

እንደሚያስተላልፍ ለማውጣት ይጠቅማል ። ሞዴሉ ትኩረት የሚደርገው ትርጉምን በመገንባት እንጅ ነጠላ ቃላትና የተገነቡ ሃረጎችን ለመለየት አይደለም (Khaokaew 2013): ይህ ሞዴል በጊዜው እየሰጠ የነበረው ተቀሜታ ከፍተኛ ነው ተብሎ ቢጠቀስም በሌላ በኩል እይታዎች ደግሞ ትችቶች ቀረቡበት ይኸውም፡- የሁለተኛ ቋንቋ አንባቢዎች ሞዴሉን ለመጠቀም በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ቃላትና አረፍተ ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ ባለመቻላቸውአንብበው መረዳት አይችሉም ። በመቀጠልም ይህ ሞዴል የአንባቢዎችን የቀደመ እውቀት የሚጠይቅ መሆኑም ሌላው የቀረበበት ትችት ነው (Zainal 2011: 10): ይህንንም መሰረት በማድረግ የታህታይ-ላዕላይ እና የላዕላይ-ታህታይ ሞዴልን በማቀናጀት መስተጋበራዊ የማንበብ ሂደት ሞዴል ተከሰተ።

### 2.7.3 መስተጋበራዊ (interactive) የማንበብ ሂደት ሞዴል

ይህ ሞዴል ከሌሎች በተሻለ መልኩ ሚዛናዊ የማንበብ ሂደትን የሚያንፀባርቅና የማንበብ ሂደቶች የተለያዩ እውቀቶችን መስተጋብር እንዲፈጥሩ የሚያደርግ ሞዴል ነው (Ling 2011 :Zainal 2011) ። ይህ የማንበብ ሂደት ሞዴል በታህታይ-ላዕላይና በላዕላይ-ታህታይ ደረጃዎች የተገናኘውንና ብዛት ያለውን የዕውቀት ምንጭ በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲዋሃድ ያደርጋል።ሞዴሉ በማመጣጠን መላምት የአንድን አንባቢ የማንበብ ሂደት ዝቅተኛ ቢሆንም የቀደመ ዕውቀቱን በመጠቀም እንደገና ለማሻሻልና ድክመትን ለማስወገድ ዕድል ይሰጣል።ሞዴሉ የተለያዩ የማንበብ ተግባራትን ለመጭረስ ወይም የተለያዩ የማንበብ አላማዎችን ለማከናዎን፤የማንበብ ብልሃትን ባግባቡ በመጠቀም የማንበብ ክሂላቸውን ማጎልበት እንዳለባቸውም ያበረታታል (Carrell 1998)::

## 2.8 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርእስ ስር የምንመለከተዉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አዕምሯዊ ብልሃቶች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያላቸውን ሚና በተመለከተ ከዚህ በፊት የተሰሩ ስራዎችን ነው፤በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች በሃገር ውስጥ እንዲሁም በሃገር ውጭ የተሰሩ ከብልሃቶችና ከአንብቦ መረዳት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ስራዎች ለማየት ይሞከራል።

ሌላው ሀገረኛ ጥናት Yohannes (2013) ‹‹ A Survey of Secondary School Students' Reading Strategy Use, Teachers' Perceptions and Practices: the Case of Grade Nine ›› ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በማንበብ ብልሀቶች ዙርያ ሲሆን፣ ካሉት ስድስት የማንበብ ብልሀት መካከሌ በአእምሮአዊ እና ሌእለአእምሮአዊ ይ

ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓማ የማንበብ ብሌሀት ትምህርትን በ9ኛ ክሌ በእንግሉዘኛ ቋንቋ ትምህርት ጊዜ በመተግበር ውጤታማነቱን መሞከር ሲሆን፣ ምን ያህሌ ተማሪዎች ይህን ብሌሀት ትምህርታዊ ጽፎችን በሚያነቡበት ወቅት ይጠቀሙበታሌ የሚለውን መመርመር ነው። እንዲሁም ጥናቱ ቅኝታዊ ጥናት ሲሆን፣ የአጠናን ዘዴውም አስተያየቶችን በመሰብሰብ እና ስሌጠና በመስጠት ነው። ከዚህም ሌላ ለመምህራን እና ለተማሪዎች የጽ መጠይቅ በማቅረብ መረጃዎችን አሰባስቧል።

እንድሪስ እና አሸናፊ (2007)‹‹የአንብቦ መረዳትብልሃቶችን መማር ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ››በሚል ርዕስ ምርምር የካሄዱ ሲሆን በጥናቱ ውስጥም ትኩረት ያደረጉት ብልሃቶች ከአንብቦ መረዳት ጋር ያላቸውን ዝምድና ከፆታ አንፃርም መመርመር ሲሆን የተጠቀሙት የመረጃ መሰበሰቢያ ዘዴዎችም የፅሁፍ መጠይቅ፣ፈተና፣ፅብረቃዎችና የእለት ማስታዎሻዎችን ተጠቅመዋል።የትንተና ዘዴዎችም ዓይነታዊና መጠናዊ ናቸው። ከምርምሩ የተገኘ ውጤትም በፆታ በኩል ብልሃቱን በመማርና ባለመማርያለውን ውጤት ለመለካት የጎላ ልዩነት እንደሌለ የታየ ሲሆን ጠቅላላ ብልሃቶችን ካልተማሩት የተማሩት የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገቡ በጥናታቸው ጠቁመዋል። ሰርካለም(2010)‹‹አፅምሯዊና ልዕለ አፅምሯዊ የማንበብ ብልሃቶች አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑተማሪዎች አማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ያለው አስተዋፅኦ›› በሚል ርዕስ የተደረገ ጥናት ሲሆን ይህ ጥናት ከጥናቴ ጋር ያለው ተያያዥነት አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ብልሃቶች የላቸውን አስተዋፅ፤ተጠኝዎች በቁጥጥርና በሙከራ ቡድን ተከፍለው መጠናታቸው፤ከትንተና ዘዴዎች ውስጥ በመጠናዊው ትኩረት ተደርጎ ውጤቱ መተንተኑና ጥናቱ ሙከራዊ መሆኑ ነው።

የሚለያየውም በክፍል ደረጃ ብልሃትን በመጠቀም በኩልአንዱ ሁለት ብልሃቶችን መጠቀሙ ሌላኛው ደግሞ አንድ ብልሃት ብቻ መጠቀሙ እንዲሁም አንደኛው በሁለተኛ ቋንቋ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መሰራቱ ለልዩነታቸው ጉልህ ነጥቦች ናቸው። እሱባለው (2010) ‹‹የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር የአንብቦ መረዳት ውጤትን ለማጎልበትና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለው አስተዋፅኦ በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት›› በሚል ርዕስ ጥናት ያደረገ ሲሆን የጥናቱ ትኩረትም አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ብልሃቶችን መጠቀሙ፤ ብልሃቶችን ቀድሞ ለተጠኝዎች እንዲማሩት መደረጋቸው፤ ጥናቱ ምርምራዊ መሆኑ ከኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው፤ በመቀጠልም ልዩነቱን ለመግለፅ ያህል የኔ ጥናት በአንድ ቋንቋ ብቻ የተሰራ ሲሆን የሱ ጥናት ደግሞ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪዎችን ማለትም አማርኛና ሱማሊኛቋንቋተናጋሪዎችን

ትኩረት አድርጎ አጥንቷል፡፡ በጥናቱ ውስጥም ስልጠናውን የወሰዱት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ተሻሽሎ መታየቱን በጥናቱ በተገለፀው ውጤት ተጠቁሟል፡፡

በውጭ ሃገር የተደረጉ ጥናቶችን ስንመለከት ደግሞ( Gu,2003a) Language learning stratiegies in reading understand) በሚለው ጥናት ውስጥ ዓላማ አድርገው የተነሱት በዋናነት ሶስቱንም ብልሃቶች ሲሆን ይኸዉም አዕምሯዊ፣ ልዕለ አዕምሯዊና የማህበራዊ ግንኙነት ብልሃቶች ናቸው፡፡የጥናቱ ተሳታፊዎችም እንግሊዝኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው በሆኑት ላይ ሲሆን ይህም ብልሃቶችን በግልፅ በማስተማር የሚመጣውን ለውጥና ከሶስቱብልሃቶች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በየትኛው የተሻለ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ የሚለው ሀሳብም በጥናቱ ዳሰሳ ተደርጎበታል፡፡ በተጨማሪም አጥኚው ጥናቱን ለመተንተን ነፃ ቲ-ቴስት ናሙናን የተጠቀሙ ሲሆን ውጤቱም ስልጠናውን የወሰዱ ተማሪዎች የተሻለ የአንብቦመረዳት ዕዉቀታቸው ሊጎለብት እንደቻለ በጥናቱተጠቁሟል፡:

Ozek &Civelek (2006) <<Astudy on use the cognitive reading strategies by ELT students>>በሚል ርእስ ምርምር ያደረጉ ሲሆን ከአዕምሯዊ ብልሃቶች ውስጥ በየትኛው ቢማሩ ለተማሪዎች ይቀላቸዋል የሚለውን ካጠኑ በኋላ ከቀረቡት አዕምሯዊ ብልሃቶች ውስጥ ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጥቅም ላይ ዉለው ትምህርቱን ውጤታማ ሊያደርጉ ይችላሉ የሚለውን ለመምረጥና በመማሪያ መፅሀፎች ላይም ተግባራዊ እንዲሆን በማሰብ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ በተጨማሪም አዕምሯዊ ብልሃቶችን ከመጠቀም ንባር የምንባብ አመራረጥ ማለትም ረዥም፣ አጭር፣ ሳቢና ማራኪ ፣አሰልቺ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣አካባቢያዊ አውድ የሚለውን አካተው በማጥናት የትኛው የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ሊያነሳሳ የሚችል መሆኑን በጥናታቸው ድምዳሜ ሰጥተዉበታል፡፡

Mehrpour et al. (2012) ‹‹ለተማሪዎች የማንበብ ብልሃትን በማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ለመፈተሽ ያለውን ጠቀሜታ›› በሚል ርእስ በተደረገው ጥናታቸው ስለ ብልሃቶች በተሰጠው ስልጠና በቁጥራቸው ትንሽ የሚሆኑ ተማሪዎች ተጠቃሚ ሆነው ስላላገኙት የብልሃቶች ስልጠና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ አላዳበረም የሚል ድምዳሜ ሰጥተዋል፡፡

Cosentino (2017) ‹‹ ብልሃቶችን ማስተማር ለደካማ አንባቢዎች ውጤታማነትና ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው አስተዋፅኦ››በሚል ባደረጉት ጥናት በብልሀቱ በተማሩና ባልተማሩ ተማሪዎች መካከል በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ላይ ምንም ልዩነት እንደሌለ በጥናታቸው ገልፀዋል፡፡

Aghael (2011). ‹‹ Cognitive and MetaCognitive Reading Strategies of Iranian EFL Learners. ›› ይህ ጥናት አማ አድርጎ የተነሳው አእምሮአዊ እና ሌእለአእምሮአዊ የማንበብ ብሌሀት እንግሉዘኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ለኢራን ተማሪዎች መግለጽ፣ እንዲሁም የአእምሮአዊ እና ሌእለአእምሮአዊ ብሌሀት ጠቀሜታ እና እነዚህን ብሌሀቶች በግሌጽ ማስተማር ለንባብ ብቃት፣ ለግሌ ውጤታማነት፣ ለብሌሀቶች ሽግግር እና ለብሌሀቶች ስሌጠና ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር ነው፡፡

በተጨማሪም Bentahar (2012).‹‹ Can ESL Teachers Teach Reading Metacognitive Strategies?›› በሚሌ ርእስ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ያጠኑ ሲሆን፣ አማ አድርገው የተነሱትም ሌእለአእምሮአዊ እውቀት ከሌእለአእምሮአዊ ብሌሀት ጋር እንደ ሚያያዜና ለማንበብ ክሂሌ ያለው ውጤታማነት ማመሌከት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ጥናቱ በዋናነት ለማየት የሞከረው ሶስቱ ሌእለአእምሮአዊ የማንበብ ብሌሀቶችን (ማቀድ፣ መቆጣጠር እና ምዘና) ነው፡፡ ጥናቱም መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመው የጽ መጠይቅ እና የአንብቦ መረት ፈተና ሲሆን፣ የጥናቱን ውጤት ለመተንተንም ነጻ ቲ-ቴስት ናሙና (Independent t- test Samples) ዘዴ ተግባራዊ ሆኗሌ፡፡ በመጨረሻም በሶስቱ ብሌሀቶች ተማሪዎች ከቅድመ ፈተናው ይሌቅ በድህረ ፈተናው ጥሩ ውጤት እንመጡ (ድህረ ፈተናው ከቅድመ ፈተናው ይሌቅ ጉሌህ የሆነ ሌዩነት እንመጣ) የጥናቱ ግኝት ያስረዲናሌ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር ነዉ፡፡ በመሆኑም የምርምሩን ዓላማ ለማሳካት መላምቶችን በመንደፍ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ ከመጠናዊ የምርምር ዘዴዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን ከፊል ፍትነታዊ የምርምር ዘዴን (quasi Expermental Research) የተከተለ ነዉ፡፡ ከፊል ፌትነታዊ ምርምር የተመረጠበት ምክንያትም በተለይ በማህበራዊ ሳይንስ ሁሉንም ተላውጣዎች ለመቆጣጠር አስቸጋሪ እንደሆነ እነ Cohen፣ Manion & Morrison (2007) እና Dyer (1995) የገለጹትን በመገንዘብ ነዉ፡፡ በተጨማሪም አጥኝዋ ይህንን ዘዴ የመረጠችበት ምክንያት ጥናቱ በሰዎች ላይ እንደመከናወኑ በጥናቱ ለመሳተፍ ፍቃደኛ የሆኑ ተጠኝዎችን ለማግኘት አመቺ ሆኖ ስላገኘችው ነዉ፡፡

በዚህ ጥናት ዉስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎችን በአዕምሯዊ ብልሃት አንብቦ መረዳትን በማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን በማጎልበት በኩል ያለውን አስተዋፅኦ ለመመርመር የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን በመምረጥና ባለ ሁለት ቡድን በመመስረት ሲሆን ይኸውም አንዱ የቁጥጥር ቡድን ሌላኛው ደግሞ የሙከራ ቡድን ነዉ፡፡ በዚህም ሁኔታ ክፍሉ ከተመረጠ በኋላ ወደ ተግባር ከመገባቱ በፊት መረጃውን በፅሁፍ መጠይቅ በማሰባሰብ ተግባሩ እንዲጀመር ተደርጓል፡፡

በሙከራውና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ያለውን ልዩነት ለመመርመር ያህል የቁጥጥር ቡድኑን መደበኛው ትምህርት በሚካሄድበት ሂደት በማስተማር የሙከራ ቡድኑን ደግሞ በተሳሳይ ፈረቃ ስልጠና በመስጠት ማለትም የመማሪያ መፅሀፉን ምንባብ በመጠቀም ና በማስተማር ሲሆን ስልጠናውን ሲወስዱም ለ6 ሳምንታት ነበር፡፡ ይኸውም በመጀመሪያዉ ሳምንት መደጋገምና መዘርዘር የሚሉት ሲሆኑ በሁለተኛ ሳምንት ደግሞ ምክንያታዊ መሆን የሚለውን በሶስተኛዉ ሳምንት ደግሞ መመርመር በአራተኛው ሳምንት መገመት በአምስተኛው ሳምንት ማለማመድ ሲሆን በስድስተኛዉ ሳምንት ደግሞ ማስትዎስና መከታተል የሚሉትን የአእምሯዊ ብልሃት ተግባራት ለተማሪዎች የንባብን አውድ በማቅረብና በግልፅ በማሰልጠን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሻሻል እና ለብልሃት

አጠቃቀማቸው የሚኖረውን አስተዋፅኦ የሚመረምር እንዲሆን ታልሞ ስልጠናው ለተማሪዎች ተሰጥቷል ።

## 3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

ጥናቱ የሚካሄደው በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ቀርሳ ወረዳ በቡልቡል ት/ቤት በሚማሩ የ2015 ዓ.ም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነዉ። በቡልቡል አጠቃላይ ትምህርት ቤት አምስት ክፍሎች ይገኛሉ። ነገር ግን ይህ ጥናት የሚያተኩርባቸው ክፍሎች በሁለቱ ሴክሽኖች ነው።

ይህ ትምህርት ቤት አመቺ የናሙና ዘዴን በመጠቀም ተመርጧል፤ምክንያቱም ትምህርት ቤቱ አጥኚዋ መደበኛ ስራዋን በምትሰራበት ቅርብ በመሆኑ በከተማው ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መረጃ ለማግኘት ያለው አመችነት ታሳቢ ተደርጎ ነዉ። የጥናቱ ተሳታፊዎች በዚሁ ትምህርት ቤት በ2015ዓ.ም የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው።

ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች መካካል የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ በአላማ ተኮር የናሙና ስልት ተመርጠዋል። እነዚህ ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት እስከ መጨረሻዉ ለማጥናት ሲባል በርግጥ ከዘጠነኛ ክፍል ይልቅ አስራ ሁለተኛ ክፍሎች የተሻለ የክፍል ደረጃ ያላቸው ቢሆኑም ግን እነዚህ ተማሪዎች የክልል አቀፍ ፈተና ተፈታኞች በመሆናቸውና ቀደም ብለው ለፈተና ዝግጅት ስለሚያደርጉ የተጣበበ ጊዜያቸውን ላለመሻማት ሲሆን በቀጣይ ደግሞ ለዝግጅት የሚፈቀድላቸውን ጊዜ ከቤታቸው ሆነዉ ስለሚጠቀሙ ከተወሰነ ጊዚ በኂላ ወደ ትምህርት ቤት ስለማይመጡ ለዚህ ጥናት አልተመረጡም።

በዚህም ሁኔታ ከቀሩት የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የተሻለ የክፍል ደረጃ ያላቸውና እስከ መጨረሻ ለማጥናት የተሻሉ የሚሆኑትን የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተመርጠዋል። በተጨማሪም አጥኚዋ ዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህርት ስለሆነች ለማጥናት አመቺ ስለሆነ አስረኛና አስራ አንደኛ ክፍሎችን ላትመርጣቸው ችላለች።

ለጥናቱ በተመረጡበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአማካይ 75 ተማሪዎች የሚማሩባቸው አምስት የመማሪያ ክፍሎች ኣሉ። ስለሆነም በዚህ ትምህርት ቤት 168 ወንድ ተማሪዎችና 207 ሴት ተማሪዎች በድምሩ 375 ተማሪዎች በዘጠነኛ ክፍል ተመዝግበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። በዚህ መሰረት በዚህ ትምህርት ቤት ከሚማሩት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 40 ፐርሰንት ያህሉ

በእድል ሰጭ የናሙና ዘዴዎች መካከል ስርዓታዊ ዘዴ (systematic sampling) በመጠቀም 150 ተማሪዎች በጥናቱ እንዲሳተፉ ተመርጠዋል፡፡ እነዚህም 73 ወንድ ተማሪዎችና 77 ሴት ተማሪዎች ናቸው፡፡ አመራረጡም በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ተማሪዎችን ስም ዝርዝር ከትምህርት ቤቱ የማህደር ክፍል ሃላፊ በናሙናነት በመውሰድ ነዉ፡፡ እንዲሁም እነዚህ ተጠኚ ተማሪዎች ብዛታቸው 150 ሲሆኑ እነዚህን ተማሪዎች በዕጣ በመለየት በሁለት ከተከፈሉ በኂለ አንደኛው ቡድን የቁጥጥር ቡድን ማለትም ወ 36 ሴ 39ድ= 75ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሙከራ ቡድን ይኸውም ወ= 39 ሴ= 36ድ= 75በማድረግ ነው፡፡

እንዲሁም እነዚህ ተጠኚ ተማሪዎች ብዛታቸው 150 ሲሆኑ እነዚህን ተማሪዎች በዕጣ በመለየት በሁለት ከተከፈሉ በኂለ አንደኛው ቡድን የቁጥጥር ቡድን ማለትም ወ 36 ሴ 39ድ 75ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሙከራ ቡድን ይኸውም ወ= 39 ሴ= 36ድ= 75በማድረግ ነው፡፡ እነዚህም ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ተመሳሳይ መሆን አለመሆናችውን ለማወቅ ተመሳሳይ ፈተና ተፈትነዋል(pre-test):: በሁለቱም ቡድኖች የተገኘው ውጤት ልዩነት ያላሳየና የተማሪዎቹም አቅም ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የጥናቱ ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች አዕምሯዊ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ማሳደግ ረገድ ያለው ሚና መመርመር ነዉ፡፡ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ፈተና ናቸው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም በተመለከተ በማንበብ ብልሃት ከመማራቸው በፊት የነበራቸውን የብልሃት አጠቃቀም ለማዎቅ ከፅሁፍ መጠይቁ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ደግሞ ፈተና ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 3.3.1 የፅሑፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ ውስጥ የፅሑፍ መጠይቅ የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤን ለመፈተሽ የሚያገለግል በመሆኑ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ አድርጎ ተጠቅሟል፡፡ የጽሑፍ መጠይቅ በዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ከተመረጡት ዘዴዎች ዉስጥ አንዱ ነው፡፡ መጠይቁ ተግባራዊ ለማድረግ የታሰበው የተሳታፊ ተማሪዎችን አዕምሯዊ ብልሃት ከአንብቦ መረዳትን ከማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለመለየት ነው፡፡ ጥያቄዎቹም የሚዘጋጁት በአዕምሯዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳትን ስልት የሚካተቱትን አጠቃላይ የማንበብ ብልሃት

ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ነው፡፡በተጨማሪም የፅሁፍ መጠይቁ ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከቅድመ ልምምዱና ከድህረ ልምምዱ ተግባር የተሰጠ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴም ነዉ ፡፡ የተዘጋጁት ጥያቄዎችም

10 ሲሆኑ አዘገጃጀቱን በተመለከተ Oxford (1990) እና Wantroba-ferrer (2011) የተጠቀሙትንና በእንግሊዝኛ የነበረውን ወደ አማርኛ ለመመለስ በመሞከር ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞረው መጠይቁን ከስልጠና በፊትና በኋላ የተሰጠ ስለሆነ መጠይቆቹ የተዘጋጁት የሊከርት የደረጃ ስኬልን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ይህ መጠይቅ የተማሪዎችን አዕምሮአዊ ብልሃት ከአምብቦ መረዳት ጋር ለመለየት የአስተማማኝነት ደረጃው ከፍ ያለ ነው፡፡

### 3.3.2 ፈተና

ፈተና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት ከሚያገለግሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ ተጠቃሽ ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት አንብቦ መረዳትን የሚለካ ፈተና አወጣጥን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም ምንባቡ በመማሪያ ክፍሉ ዉስጥ ለተማሪዎች በሚቀርብበት ጊዜ መስፈርቶችን መሰረት አድርጎ እንደሆነ Stevic (1995) የገለፁት መስፈርት ከግንዛቤ በማስገባት ፈተናዎች ተዘጋጂተዋል፡፡ መስፈርቶቹም የምንባቡ ባህላዊነት፣ፍላጎት አነሳሽነት፣አሳታፊነትና አውድ የሚሉት ከግምት ውስጥ የገቡ ናቸው፡፡ ለፈተና የተወሰደው ምንባብ መካከለኛ መጠን ያለው ቢሆንም አሰልቺ እንዳይሆን ግን በአመራረጥ ሂደቱ ውስጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም የጥያቄዎቹ ብዛት በሁለት መመሪያ የተከፈሉ ሲሆን ይኸውም መመሪያ 1) እውነት ሀሰት መመሪያ 2) ምርጫ ሌላው ምንባብ በተመሳሳይ በሁለት በሁለት መመሪያ ተከፍሎ ምረጫና የቃላትን ተቃራኒ በመፈለግ ክፍት ቦታውን መሙላት የሚሉ ናቸው፡፡ ከእያንዳንዱ የወጡ ጥያቄዎች ጠቅላላ ብዛታቸው አስር አስር ናቸው፡፡ የጥያቄዎቹም አዘገጃጀት በሚመለከትም የክፍል ደረጃውን ስርዓተ-ትምህርት መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡

#### 3.3.2.1 የፅሑፍ መጠይቅ አስተማማኝነትናትክክለኛነት

በመጠይቁ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች የሚፈለጉትን መረጃ ማስገኘታቸውን ለመፈተሽ የክሮንባክ አልፋ ዘዴን የአስተማማኝነት መለኪያ ፎርሙላ በመጠቀም አሰተማመኝነቱ ተለክቷል፡፡የዚህ ጥናት የፅሑፍ መጠይቆች በOxford (1990) እና Wantroba-ferrer (2011) አስቀድሞ በተግባር ላይ የዋሉ በመሆናቸው የተወሰኑ ናሙናዎችን በመውሰድና በማስተማር ረዥም አመት ልምድ ባላቸው ሶስት አጋር መምህራን በማሳየት የተወሰነ

አስተያየት ተሰጥቶበትና በአስተያየቱ መሰረት ለማሻሻል በመሞከር ለጥናቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ከላይ እንደተየቀሰው በፅሁፍ መጠይቁ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች መረጃ ለመስጠት በሚችሉበት መንገድ አስተማማኝነታቸው ተለክቶ መቀመጡ አስፈላጊ ስለሆነ ይህንንም በአስተማማኝነት መለኪያ ቀመር በSPSS ተሰልቶ 0.882 በመምጣቱ መጠይቁ አስተማማኝ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

### 3.3.2.2 የቅድመና የድህረ-ፈተና አስተማማኝነት እና ትክክለኛነት

Brown (1994) ትክክለኛነት ማለት አንድን ሊለካ የተፈለገ እውቀት ወይም አላማ በአስረጂ ሁኔታ ለመለካት ከተቻለ በይዘቱ ውስጥ ትክክለኛነት ተንፀባርቋል ለማለት የሚያስችል ሲሆን አስተማማኝነት ደግሞ አንድን መረጃ ለመሰብሰብ በታሰበው መንገድና በተገቢው ሁኔታ ለመሰብሰብ እንደተቻለ ለማወቅ የምንችልበት ነዉ በማለት ገልፀዋል፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚዋ ቅድመናድህረ-ፈተና ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎችን በተማሪዎች ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ መረጃ ማስገኘት መቻላቸውን ወይም አለመቻላቸውን ፈትሻለች፡፡ በዚህም ሁኔታ ይህ ጥናት የፈተናን አስተማማኝነት ለመለካት በቲ ቴስት መለኪያ ቀመር እንዲለካ ተደርግል፡፡ ትክክለኛነቱም በተመሳሳይ የፒርስንን መለኪያ በመጠቀም የተለካ መሆኑንም በአጋር ባለሙያዎችና በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለፈተናና ምዘና ኮሚቴዎች እንዲታይ ተደርጓል፡፡ የቅድመ ፈተና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ፈተናው በፒርሰን መለኪያ ዘዴ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 0.994 በመምጣቱ ፈተናው አስተማማኝነቱን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ድህረ ፈተናውም በተመሳሳይ ዘዴውን በመጠቀም ሲታይ ስሌቱ 0.993 ስለመጣ የአስተማማኝነት ብየና (T-test realability) ተረጋግጧል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከተሳታፊዎቹ የተገኙት መረጃዎች ከተመዘገቡ በኋላ ለትንታኔ ከመቅረባቸው በፊት መልሶቹ በትክክል መሞላታቸው ይጣራል፡፡መረጃዎችም ለትንታኔ በሚያመች መልኩ ኮድ ተደርገው በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ (code sheet) ላይ እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡ መረጃዎቹ እንደየባህሪያቸው ተለይተውና አስፈላጊውን ማጣራት ከተደርገባቸው በኋላ ወደ ትንተናው ተገብቷል፡፡ ይኸውም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት አቅም ደረጃ፣ከልምምድ በኋላ የሚያመጡትን ለውጥና ችሎታ ለመፈተሽ የተተነተነ ሲሆን ትንተናው የተተነተነውም በT-test በSPSS software በመጠቀም ሲሆን የምንባቡ አይነት ከምንባቡ የወጡ ቃላትን አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ የሚያደርግ የሚመቹ ናቸው፡፡ ሌላው የፈተናውን

ስልት በተመለከተ የችሎታ መለኪያ ፈተና ይሆናል፡፡ ይህ የሆነውም ልጆቹ ካነበቡት ነገር ስለቃላት ያላቸውን የቃላት ችሎታ የሚመለከት ጥያቄዎች ምን ያህል ተረድተውና ካሁን በፊት ያላቸውን የቃላት ዕውቀቶች ችሎታ ሊጠቀሙበት ይችላሉ የሚለውን ሊለካ ይችላል ተብሎ ስለታመነበት ነው፡፡

## 3.5 የጥናቱ ስነ-ምግባራዊ ሁኔታ

ይህን ጥናታዊ ስራ ለማከናወን የተለያዩ ተግባራት ተተግብረዋል ከነዚህም ለመጥቀስ ያህል የተለያዩ መርጃዎችን ለመሰብሰብ ያመች ዘንድ የትምህርት ክፍሉ ለሚመለከታቸዉ ባለ ድርሻ አካላት አስፈላጊዉን ትብብር እንዲደርግ ደብዳቤ ፅፏል፡፡ ደብዳቤዉንም ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት በመዉሰድ ትብብር እንዲደርግ ተጠይቋል፡፡ በቀጣይም 9ኛ ክፍልም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን በርዕሰ መምህሩ አማካኝነት በማሰባሰብና ሀሳቡን ግልፅ በማድርግ አጠር ያሉ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በመምህራኑ አማካኝነትም ለጥናቱ ተፈላጊ የሆኑ ተማሪዎች ጋርም በመገናኘት ስለ አላማዉ ግልፅ ውይይት ተደርጓል፡፡ ለጥናቱ በተመርጡ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ወደ ተግባር ከመገባቱ በፊት የፀሁፍ መጠይቅ ተጠይቀዋል ለተጠኝ ተማሪዎችም ምርምሩ ላይ ለሚሰበሰብ ማንኛውም ውጤት በነሱ መደበኛ በሆነው የክፍል ውጤታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደማይኖርው በግልፅ ለማስርዳትና ለመግባባት የተቻለበት ሁኔታ ተከናውኗል:: ጠቅለል ሲል በጥናቱ ዙሪያ ለሚከናወኑ ማንኛውም አይነት መረጃዎች የተማሪዎቹን ፍቃድ በመጠየቅ መረጃውን መሰብሰብ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ ውጤት ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተና

ከላይ በቀረቡት ምዕራፎች እንደተገለፀው ጥናታዊ ፅሑፍ የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ውጤት መጎልበትና የብልሃት አጠቃቀማቸውን በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው፡፡የጥናቱ ዋና አላማ ለዋናው ጥናት የቀረቡትን መሰረታዊ ጥያቄዎች መመለስ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጥናቱ አሰራር ቅደም ተከተሎች የመረጃ አተናተኖች ባጠቃላይ የጥናቱ ስነ ዘዴ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ ለመፈተሽ የተገኘውን ውጤት ማንፀባረቅና መፍትሔዎችንም መጠቆም የመከተሉትን ሃሳቦች ማመላከት ነው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ፅሑፍ ውስጥ የፅሑፍ መጠይቅ የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤን ለመፈተሽ የሚያገለግል በመሆኑ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ አድርጎ ተጠቅሟል፡፡ የጥናቱ መረጃዎች በጽሑፍ መጠይቅ እና በፈተና ተሰበስበዋል፡፡ለአተናናተን እንዲሁም ለአቀራረብ ያመች ዘንድ መረጃዎቹ በሁለት ተከፍለው ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡የመጀመሪያው የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የቅድመ እና የድህረ ትምህርት ፈተናዎች ትንተና የሚተነተንበት ክፍል ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 1. የጽሑፍ መጠይቅ አንድ**

## 4.2 ጽሑፍ መጠይቅ አንድ ስልጠናውን ከመውሰዳቸው በፊት ለተማሪዎች የቀረበ መጠይቅና ትንተና

| ተ.ቁ | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | 20 | 16.7 | 10 | 8.3 | 80 | 66.7 | 10 | 8.3 |
| 2 | 4 | 3.3 | 2 | 1.67 | 95 | 79.2 | 19 | 15.8 |
| 3 | 5 | 4.2 | 3 | 2.5 | 102 | 85 | 10 | 8.3 |
| 4 | 78 | 65 | 30 | 25 | 10 | 8.3 | 2 | 1.67 |
| 5 | 69 | 57.5 | 30 | 25 | 14 | 11.67 | 7 | 5.8 |
| 6 | 89 | 74.2 | 28 | 23.3 | 2 | 1.67 | 1 | 0.83 |
| 7 | 71 | 59.2 | 31 | 25.8 | 10 | 8.3 | 8 | 6.67 |
| 8 | 2 | 1.67 | 8 | 6.67 | 80 | 66.7 | 30 | 25 |
| 9 | 70 | 58.3 | 45 | 37.5 | 5 | 4.2 | - | - |

<u>መግለጫ</u>፡- 1.እስማማለው 2.በጣም እስማማለው 3.አልስማማም 4. በጣም አልስማማም

ከሰንጠረዥ 1 እንደምንረዳው ሳነብ የማነበውን ንባብ በቀላሉ እረዳዋለው ለሚለው 80(66.7%) አልስማማም ያሉ ሲሆን 20(16.7%) ብቻ እስማማለው ብለዋል፡፡ እንዲሁም በዚህው ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር 2 የማነባቸው ምንባቦች የምረዳቸው በየአንቀጹ ነው የሚለውን 4(3.3%) እስማማለው ሲሉ 2(1.67%) በጣም እስማማለው ብለዋል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ 95(79.2%) እና 19(15.8%) በቅደም ተከተል አልስማማም እና በጣም አልስማማም ያሉ ናቸው፡፡ በዚህው ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር 7 ማንበብ ያለብን የምንማረውን ትምህርት ብቻ ነው ለሚለው 71(59.2%) እስማማለው ሲሉ 31(25.8%) በጣም እስማማለው ብለዋል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ 10(8.3%) እና 8(6.67%) በቅደም ተከተል አልስማማምና በጣም አልስማማም ያሉ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ በዚህ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር 8 እንደተገለፀው ሳነብ ያልተረዳዋቸውን ቁልፍ ቃላቶች ሁልጊዜ መዝገበ ቃላት እጠቀማለሁ ለሚለው 2(1.67%) እስማማለው ያሉ ሲሆን 8(6.67%) ያህሉ ደግሞ በጣም እስማማለው ያሉ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ 80(66.7%) እና 30(25%) በቅደም ተከተል አልስማማምና በጣም አልስማማም ያሉ ናቸው፡፡ በዚህ ሰነሰጠረዥ የፅሑፍ መጠይቅ እንደምረዳው ተማሪዎች የሚያነቡት በሚማሩት ትምህርት ብቻና በሚያነቡበት ጊዜ መዝገበ ቃላት ከመጠቀም ይልቅ ግምታዊ ትርጉም እንዲሚሰጡ ያሳያል፡፡

**ከሰንጠረዥ 2. የፅሑፍ መጠይቅ ሁለት**

## 4.3 ተማሪዎች ስልጠናዉን ከመዉሰዳቸው በኋላ የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅናትንተና

| ተ.ቁ | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | - | - | - | - | 3 | 37.5 | 5 | 62.5 |
| 2 | - | - | - | - | 6 | 75 | 2 | 25 |
| 3 | - | - | - | - | 7 | 87.5 | 1 | 12.5 |
| 4 | - | - | - | - | 6 | 75 | 2 | 25 |
| 5 | 1 | 12.5 | - | - | 7 | 87.5 | - | - |
| 6 | 1 | 12.5 | 2 | 25 | 5 | 62.5 | - | - |
| 7 | 1 | 12.5 | 3 | 37.5 | 4 | 50 | - | - |
| 8 | 5 | 62.5 | 1 | 12.5 | 2 | 25 | - | - |
| 9 | 6 | 75 | 1 | 12.5 | 1 | 12.5 | - | - |
| 10 | 6 | 75 | 1 | 12.5 | 1 | 12.5 | - | - |

<u>መግለጫ</u>፡-1.እስማማለሁ 2.በጣም እስማማለሁ 3.አልስማማም 4. በጣም አልስማማም

በሰንጠረዥ 2 እንደሚያመለክተው የተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት ከፍተኛ ነው በሚለው 3(37.5%) ያህሉ አልስማማም ሲሉ 5(62.5%) ያህሉ ደግሞ በጣም አልስማማም ያሉ ነቸው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የምንባቡን ፅንሰ ሃሳብ በቀላሉ ይረዱታል ለሚለው 6(75%) ያህሉ መምህራን አለስማማም ሲሉ 2(25%) በጣም አልስማማም ብለዋል፡፡ ተማሪዎች የምንባብ ፈተና ሲፈተኑ በጣም ደስተኛ ናቸው በሚለው 7(87.5%) ያህሉ መምህራን አልስማማም ያሉ ሲሆን 1(12.5%) በጣም አልስማማም ብለዋል፡፡ ከዚህ መልስ እንደምንመለከተው ተማሪዎች የማንበብ ልምድና ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ ተማሪዎች እያንዳንዱ የንባብ ፅንሰ-ሃሳብ እንዲለዩ መርዳት የመምህራን ሙያዊ ሃላፊነት ነው በሚለው 1(12.5%) እና 2(25%) በቅደም ተከተል እስማማለው እና በጣም እስማማለው ያሉ ሲሆን 5(62.5%) ያህሉ አልስማማም ብለዋል፡፡ይህ የሚያመለክተው ተማሪዎች አንድን ንባብ አንብበው ለመረዳት በሚያስፈልጋቸው እገዛ የመምህራን ግንዛቤ አናሳ መሆኑን ነው፡፡

መምህራን ለተማሪዎች በመፅሐፋቸው ያለውን የምንባብ መልመጃዎች ዘውትር ይሰጣሉ በሚለው 3(37.5%) በጣም እስማማም ያሉ ሲሆን 4(50%) ያህሉ ደግሞ አልስማማም ያሉ ናቸው፡፡ ይህ የሚያመለክተው ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ክሂላቸው እንዳይዳብር የመምህራን አሉታዊ አስተዋፅኦ እንዳለበት ያሳያል፡፡

## 4.4 በፈተና የተገኘ ውጤትትንተና

### 4.4.1 ከቅድመ -ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎችትንተና

**በሰንጠረዥ-3.ከቅድመ-ትምህርት ፈተና የተገኙ ከፍተኛ፤ ዝቅተኛ ፤አማካይ ውጤት፤መደበኛ ልይይትና ቲ-ቴስት**

| የፈተና አይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | T-test | df | የጉልህነት ደረጃ (Pvalue) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | የሙከራ ቡድን | 75 | 25 | 50 | 33.7 | 0.48 | 1.6 | 74 | 0.109 |
| | የቁጥጥር ቡድን | 75 | 25 | 50 | 33.8 | | | | |

$p>0.05$

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከትነው ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅድመ-ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት ዝቅተኛ ውጤት 25 ሲሆን ከፍተኛ ውጤት ደግሞ 50 ነው፡፡ የሙከራ ቡድን አማካይ ውጤት 33.7 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ደግሞ 33.8 ነው፡፡ መደበኛ ልይይታቸውም 0.48 ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው በቅድመ-ትምህርት ፈተና በሁለቱም ቡድኖች መካከል ያለው ልዩነት ጠባብ መሆኑን ነው፡፡

### 4.4.2 የድህረ-ትምህርት ፈተና የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**ሰንጠረዥ 4. ከድህረ-ትምህርት ፈተና የተገኙ ከፍተኛ፤ ዝቅተኛ ፤አማካይ ውጤት፤ መደበኛ ልይይትና ቲ-ቴስት**

| የፈተና አይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | ዝቅተኛ ውጤት | ከፍተኛ ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | T-test | Df | የጉልህነት ደረጃ(P-value) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድህረ-ትምህርት ፈተና | የሙከራ | 75 | 30 | 67 | 40.4 | 10.01 | 4.04 | 74 | 0.000 |
| | የቁጥጥር | 75 | 23 | 60 | 34.4 | 7.1 | | | |

$P<0.05$

የተማሪዎች አዕምሯዊ መማር ብልሃት ልምድ ማሰልጠን ከአምብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ዝምድና ለመፈተሽ የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን ተከታታይ የሆነ የምንባብ ዘዴዎችን ለአምስት ጊዜ በመስጠትናበማስተማር ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ ለተመሳሳይ ጊዜ በመደበኛው የመማር ማስተማር ዘዴ በመስጠት ተመሳሳይ ፈተና እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ እንደተቀመጠው ውጤቱ ተገኝቷል ማለት ነው፡፡

በሰንጠረዥ -4 እንደተመለከትነው የሙከራ የጥናቱ ተሳታፊዎች በድህረ-ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት ዝቅተኛ ውጤት 30 ሲሆን ከፍተኛ ውጤት ደግሞ 67 ነው፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድን ያስመዘገቡት ዝቅተኛ ውጤት 23 ሲሆን ከፍተኛ ውጤት ደግሞ 60 ነው፡፡ የሙከራ ቡድን አማካይ ውጤት 40.4 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ደግሞ 34.4 ነው፡፡ መደበኛ ልይይታቸው ደግሞ የሙከራ ቡድን 10.01 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን 7.1 ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው በድህረ-ትምህርት ፈተና በሁለቱም ቡድኖች መካከል ያለው ልዩነት የሰፋ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በሁለቱም ቡድኖች መካከል የታየው ልዩነት በስታትስቲክስ ጉልህነት ያለው ስለመሆኑ መረጋገጥ ስላለበት ለዚህ ሲባል የዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህ መሰረት በ74 የነፃነት ደረጃ (ቲ-ቴስት=4.04, የፒ ዋጋ (0.000) ከመቁረጫ ነጥብ (0.05) አንሶ በመገኘቱ በሁለቱ መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት መኖሩን መረዳት ይቻላል።ይህም ለውጥ ከሙከራ በኋላ የመጣ መሆኑን ያሳያል።

## 4.5 የውጤት ትንተናው ማብራሪያ

በጥናቱ አላማ ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ይህ ጥናት የተካሄደበት ዋና አላማ አዕምሯዊ የማንበብ ብልሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ሚና ምን እንደሆነ መመርመር ነበር። ስለሆነም የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ የብልሃቱ ተግባራዊነት መፈተሽና ውጤታማነቱን በማረጋገጥ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፍ ማድረግ ነው።

መረጃውን ለማቅረብና ለመተንተን ያመች ዘንድ የጥናቱ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ ከፈተናና ከፅሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን አማካይ እና መደበኛ ልይይት ከወጣላቸው በኋላ በሙከራና በቁጥጥር ቡድን መካከል ያለውን የውጤት ልዩነት በመደበኛ ልይይት፣በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልተው ቀርበዋል። ይኸውም በቅድመ ፈተና ትምህርት የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤት 33.7 እና 33.8 በቅደም ተከተል የነበረ ሲሆን በድህረ ፈተና ትምህርት ደግሞ 40.4 እና 34.4 በቅደም ተከተል ሊሆን ችሏል።እንዲሁም መደበኛ ልይይታቸው በቅድመ-ፈተና ትምህርት 0.48 10.01 እና 7.1 በቅደም ተከተል ለመሆን ችሏል ማለት ነው። በጨረሻም የቲ-ቴስት ዋጋቸውንና የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ስንመለከት በቅድመ-ፈተና ትምህር ትላይ -1.6 እና 1.09 ሲሆን በድህረ-ፈተና ትምህርት 4.04 እና 0.000 በቅደም ተከተል መሆን ችሏል። ከዚህ በላይ የተመዘገበው ውጤት እንደሚያሳየው ተማሪዎችን በተለመደው የመማር ማስተማር ከማስተማር ይልቅ በሙከራ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያሻሽለዋል። በተማሪዎች ለታየው መጠነኛ የአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ለታየው ልዩነት ምክንያት የሆነው አዕምሯዊ ብልሃት ስለሆነ ተማሪዎችን በዚህ ዘዴ አንብቦ መረዳትን መሰረት አድርጎ ማስተማር የተሻለ ለመሆኑ ማረጋገጫ ይሆናል። ይህንንም አሰደግፎ ለመግለፅ ያህል(Alexander fox(2008)) Walas (1992) Brown(1984) Ozec and civelec(2006) Devis(1995) Armbster and Isborn(2002) አንብቦ መረዳትን በማስተማር በኩል በተማሪዎች ዘንድ ለውጥ ለማምጣት በብልሃቶች አሰደግፎ ማስተማር ዕውቀታቸውን ሊያዳብር ይችላል ከሚለው የጥናት ውጤት ጋር ተያያዥነቱን አሳይቷል።

ከትንተናው በተገለፀው ስሌትም አዕምሯዊ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የተሻለ እንደሆነ የሚያሳይ በመሆኑ Mehrpour et al.(2012) Cosentino(2017) እና Barnett(1988) አንብቦ መረዳትን ወይም የማንበብን ትምህርት በብልሃቶች አስደግፎ ማስተማር በተማሪዎች ችሎታ ላይ የተሻለ ውጤት አያሳይም ከሚሉት አጥኚዎች ሃሳብ ጋር የሚቃረን ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፤መደምደሚያ እና የመፍትሄ ሃሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት አንብቦ የመረዳት ብልሀቶችን በግልፅ ማሰልጠን 9ኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማዳበር የሚኖረዉን አስተዋፅኦ በመግለፅ በኩል አልሞ የተነሳ ሲሆን በምርምሩ የተነሱ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስና አላማዎችን ለመፈተሽም ጥናቱን በሚከተለዉ መንገድ ማጠቃለል ተችሏል የጥናቱ ስልት በሁለት ቡድኖች ቅድመና ድህረ ትምህርት፣ ከፊል ምርምራዊ ንድፍ ላይ የተመሰረተ ነዉ። በዚህም መሰረት ጥናቱን ለማከናወን በጅማ ዞን ቀርሳ ወረዳ ከሚገኘዉ በቡልቡል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና ተመርጧል በዚህ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በመማር ላይ በነበሩት የ9ተኛ ክፍል የመማሪያ ክፍሎች ዉስጥ በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ በሁለት የመማሪያ ክፍል ዉስጥ የሚማሩ መደበኛ ተማሪዎች ተመርጠዉ እንደቅደም ተከተላቸዉ የናሙናዉና የዋናዉ ጥናት ተሳታፊዎች ሁነዋል ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ ያገለገሉት መሳሪያዎች አንብቦ መርዳትን ለማሻሻል አስፈላጊ ብልሀቶችን አጠቃቀም መለኪያ የሚሆን የፅሁፍ መጠይቅና ፈተና ናቸዉ የሁለቱ መሳሪያዎች ተገቢነት እንዳስፈላጊነቱ በቋንቋ መምህሮችና በትምህት ቤቱ የስርአተ ትምህርት ኮሚቴዎች ተፈትሻል። ከአስተማማኝነቱ አንፃር ሰለ ፈተና ስልጠና በወሰዱ የወረዳዉ ባለሞያዎች ካሉበት ድረስ ሄዶ በማማከር የተለያዩ ሞያዊ ምክሮችን በ መቀበልና በማስተካከል አስተማማኝነቱ ተለክቶ እና ተረጋግጦ በተግባር ላይ ዉሏል ከዚህ ተያይዞ መጠይቁም ሆነ ፈተናዎች ተሰልተዉ የሚተነተኑት በነፃ ናሙና ቲ- ቴስት ነዉ።

በመቀጠልም ካሉት የመማሪያ ክፍሎች ዉስጥ ሁለት ክፍሎች ተለይተዉ የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ሆነዉ ተለይተዋል ። አንዱን ክፍል መደበኛዉ በሚማርበት ሂደት በማስተማር አንብቦ በመረዳት በኩል ጥሩ አስተዋፅኦ አላቸዉ ተብለዉ በጥናቱ የታመነባቸዉን ብልሀቶች የሚመለከቱ ትምህርቶችን በመስጠት ለሌላኛዉ ደግሞ ማለትም ከተመረጡት የቀረዉን አንዱን ክፍል ተማሪዎች ደግሞ ስልጠና ከመስጠት በፊት ለሁለቱም እኩል የሆነ ፅሁፍ መጠይቅ ተዘጋጅቶ ቀድመዉ ተጠይቀዋል ። በሁለቱ ክፍል ዉስጥ የተገኘዉ ስሌት ሲታይ ልዩነቱ ብዙ አይደለም። ሆኖም ግን ከመጠይቁ በኋላ ለአንዱ ክፍል ብቻ ስልጠናዉ ተሰጥቶ ለሌላኛዉ ደግሞ በመደበኛው ትምህርት አሰጣጥ መሰረት ለ6 ሳምንታት የተካሄደዉን ትምህርት ወስደዋል በተወሰደዉ ናሙና መሰረት በቲ-ቴስት በመተንተንም በመካከል ያሉትን ልዩነትቶችና የጥንካሬ ደረጃዎችን

ለማረጋገጥ  አገልግሏል፡፡ ጠቅለል ሲል የጥናቱ ውጤት ያሳየው ለአንብቦ  መረዳት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ብልሀቶችን ማለትም በዚህ ጥናት የተተገበሩት መደጋገም፣ ምክንያታዊ መሆን፣ መመርመር፣ መዘርዘር፣ መገመት፣ መለማመድ፣ ማስታወስ እና መከታተል የሚሉተትን የአዕምሮአዊ ብልሀት ተግባራት ለተማሪዎች በግልፅ ማሰልጠን የተማሪዎችን የብልሀት ግንዛቤና አጠቃቀም ለማሳደግ እንዲሁም ተማሪዎችን ከተለመደው የአንብቦ  መረዳት ማስተማሪያ ዘዴ በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለዉ መሆኑ ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ  የብልሀቶችን አጠቃቀምና አንብቦ የመረዳት ችሎታን አያይዞ በግልፅ ስልጠናመስጠት ንባብን ለማስተማር አገልግሎት ላይ ቢውል ሚናው የላቀ ነው፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

በጥናቱ የውጤት ትንተና መሰረት ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ  መድርስ ተችሏል፡፡ ይኸውም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በድህረ ት/ት ያስመዘገቡት አንብቦ የመርዳት ችሎታ አማካይ ውጤት በተለመደው የአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት ሲታይ የሙከራው ቡድን በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ታይቷል፡፡ በዚህም ብልሀቶችን በግልፅ ማሰልጠንእናማስተማር የተማሪዎችን ብልሀቶች አጠቃቀምን  በማሳደግና የአንብቦ መረዳት ችሎታን በማጎልበት የላቀ  አስተዋፅኦ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም በአንብቦ መረዳት  ሂደት የተማሪዎችን የንባብ ትምህርት ብልሀቶች አጠቃቀም  በማጎልበት  በተግባር ላይ እንዲልውና እንዲሰራበት የሚል የጥቆማ አንድምታን ያሳያል፡፡

## 5.3 የመፍትሄ ሀሳብ

አእምሮአዊ ብሌሀቶችን ተግባራዊ በማድረግ ብልሀቶቹ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል የሚኖራቸውን ውጤታማነት ለመፈተሽ ተሞክሯል። ከዚህ አንፃር ጥናቱ በግኝቱ መሰረት ያንፀባረቀውን የመፍትሄ ሀሳቦች ሊሰሩ የሚገባቸውን የምርምር አቅጣጫዎች አመላክቷል።

- ❖ ይህ ጥናት ለወደፊት በመደበኛ የትምህርት ሂደቱን እንዲሰራበት በመማሪያ መፅሀፍቶች ተካቶም በሁሉም ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ ቢሆን
- ❖ ጥናቱ አንብቦ መረዳትን በማጎልበት ረገድ ያለዉ አስተዋፅኦ ይበልጥ ጎልቶ መታወቅ ይችል ዘንድ በሌላ አጥኚ ጥናቱ እንደገና ቢሞከር
- ❖ በብልሀቶች አጠቃቀምና አተገባበር በኩል ለመምህሮች በባለሞያ የተደገፈ ስልጠና ቢሰጥ
- ❖ በዚህ ጥናት ግኚት  መሰረት በሙከራ ቡድኑ እና  በቁጥጥር ቡድኑ መካከል በሁሉም ክፍሎች ወንድና ሴት ተማሪዎች በየክፍሉ ነጣጥሎ  በመስራት በኩልም ዉስንነት ስላለ  በተመሳሳይ አጠናን  ዘዴ ያታን በተመለከተ ቀጣይ ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን  መገንዘብ ያሻል።

# ዋቢዎች (Reference)


ይገረሙ፡፡ (2002)፡፡ ‹‹የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት) ›› የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሰርካለም (ያልታተመ) ፡፡

ሰዓዳ የኑስ (2010) ....በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የልዕለአምሮአዊ የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ፡፡ተዛምዶ፡፡ለሁለተኛ ድግሪማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ባህር ዳር፡፡ (ያልታተመ)

እሱባለዉ ወልደገብርኤል (2010): የማንበብ ብልሃትን በግልፅ ማስተማር አንብቦ የመረዳት ዉጤትን ለማጎልበትና ለማንበብ ብልሃት ሽግግሮሽ ያለዉ አስተዋፅኦ፤በ9ኛ ክፍል ሶማልኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡

እንድሪስ አባይ (2000)....የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መማር ከአንብቦ መረዳትችሎታ ያለው ተዛምዶ፡፡ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ባህር ዳር፡፡ (ያልታተመ) ፡፡

ወይንሸት ግርማ (2007)፡፡ በአርሲ ዞን በጎልቻ ወረዳ በጫንጮ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤትበ9ኛክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ማህበረስሜታዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበትረገድ ያለው ሚና፡፡ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ ባህር ዳር፡፡ (ያልታተመ) ፡፡

ዘውዱ መብሬ፡፡ (2008) ‹‹ሚናለዋጭ ዘዴ (Reciprocal Teaching) የአማርኛ አፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትን ችሎታና የማንበብን ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋፅኦ፡በሰባተኛ ተማሪዎች ተተኳሪነት››፡፡ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ አዲስአበባ፡፡ (ያልታተመ)

ይሁኔ ገበየሁ፡፡(2009)፡፡‹‹ልዕለአእምሮአንብቦ የመረዳት ዘዴ የማንበብ ክሂልን ለማጎልበት ያለው ሚና››፡ ፡ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ባህር ዩኒቨርሲቲ፣ባህር ዳር፡፡ (ያልታተመ)

ይብሬ ጌጡ (2008) ፡፡ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ባህር ዳር (ያልታተመ) ‹‹በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የራስመርመማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ››፡፡

ያለዉ እንዳወቅ። (2006) ።የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር ። አዲስ አበባ ። አልፋ አሳታሚዎች።

Ab Manan; N.A, Alias A.A; Yusof.j and pandian, A (2011) the effects of Language Learning strategy (LLS) Training on ESL college students’ strategies used .Gading business and management used .gading business and management journal.

Alexander; A and fox, E (2008) .Reading in perspective. Infresch, M(Ed). An essential History of current Reading practices. Newark; International Reading Association Inc. pp.12-32

Anderson.N.J (1991). IndividualDifferences in Strategy Use in Second Language Reading and Testing. The Modern Language Journal, 75 (4): 460-472

Ambusratc Blehr, osbora, (2001) put reading first: the research building Blokes for teaching children to read Jessup, M.D, international institute for literacy.

Barnett, M, A (1988). Reading through context; How real and perceived strategy affects

L2comprehension .The Modern Language Journal

Bachman, L.F (1990) Fundamental consideration in Llanguage Testing.oxford and New York: oxford university press.

Brown H.D (1994). Principles of Language Learning and Teaching Cambridge; Cambridge University prentice Hall.

Carrel, P.L. (1998). Introduction .incarrelsP.L.Devine.JandHeskey. DE (Eds.), interactive Approach femtosecond Language Reading (PP.1-5). Cambridge: Cambridge university press.

Cosentino, C. L. (2017). The Effects Of Self- Regulation on Reading Comprehension, 173 Motivation for Learning, and Self- Efficacy with Struggling Readers, Western Connecticut State University; Department of Education and Educational; PhD; (Unpublished)

Davies, F. (1995) .introducing Reading. Cambridge university press.

Grabe, W., and Stoller, F. (2008). Teaching and Researching Reading. London: Pearson Education.

GU, y. (2003) ‹‹vocabulary learning in a second Language: person, Task context and strategies››. Teaching English as a second Language.

Harmer, J (1994) the practice of English language teaching. London Longman press.

Harmer, J. (1991).The practice of English language teaching. New York; Longman.

Kgabo l.b (2014) reading comprehension strategies: the use of prior knowledge as a cognitive strategy by grade 6 learners in a primary school in the lephalale area adissertation submitted in partial fulfillment of the requirements for the degree of arts in English studies. in the faculty of master humanities languages and communication studies school of at the university of Limpopo.

Khaokaew, B. (2013). An Investigation of Explicit Strategy Instruction on EL Reading of Undergraduate English Majors in Thailand University of Bedfordshire. (Unpublished Dissertation).

Ling, S. (2011). Investigation Chinese English Majors Use of Reading Strategies. A Study on the Relationship between Reading Strategies and Reading Achievements. Sweden, Tutor: Carita Lundmark. Kvistianstad University. EN 2460 Level 1V English, School of Teaching Education.

Nunan. D. (1991) .Language Learning Methodology .London: prentice Hall.

Nuttall,c (1996).Teaching Reading skills in a foreign Language (2nd Ed) .oxford Heinemann.

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ

### የጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ ትንተና በተማሪዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሳነብ የማነበውን ምንባብ በቀላሉ እረዳዋለሁ | | | | |
| 2 | የማነባቸው ምንባቦች የምረዳቸው በየአንቀፁ ነው | | | | |
| 3 | የምንባብ ፈተና ሲሰጠኝ ደስ ይለኛል | | | | |
| 4 | ምንባብ ራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው | | | | |
| 5 | የምንባቡን ፅንሰ ሃሳብ ለመረዳት የማንበብ ክሂል አያስፈልግም | | | | |
| 6 | አንድን ፅሑፍ አንብቦ ለመረዳት ደጋግሞ ማንበብ ያስፈልጋል | | | | |
| 7 | ማንበብ ያለብን የምንማረውን ትምህርት ብቻ ነው | | | | |
| 8 | ሳነብ ያልተረዳዋቸውን ቁልፍ ቃላቶች ሁልጊዜ መዝገበ ቃላት እጠቀማለሁ | | | | |

## አባሪ ለ

### የጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ ትንተና በመምህራን

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች የማንበብ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው | | | | |
| 2 | ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የምንባቡን ፅንሰ ሃሳብ በቀላሉ ይረዱታል | | | | |
| 3 | ተማሪዎች የምንባብ ፈተና ሲፈተኑ ደስተኛ ናቸው | | | | |
| 4 | የተማሪዎች የምንባብ ልምድ ከፍተኛ ነው | | | | |
| 5 | የተማሪዎች የንባብ ልምድ በተፈጥሮ የተቸራቸው እንጂ በልምምድ የሚመጣ አይደለም | | | | |
| 6 | ተማሪዎች እያንዳንዱ የንባብ ፅንሰ-ሃሳብ እንዲለዩ መርዳት የመምህራን ሙያዊ ሃላፊነት ነው | | | | |
| 7 | መምህራን ለተማሪዎች በመፅሐፋቸው ያለውን የምንባብ መልመጃዎች ዘውትር ይሰጣሉ | | | | |
| 8 | በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የሚዘጋጀው ምንባብና የምንባቡ መልመጃዎች ከተማሪዎች የክፍል ደረጃና አቅም ጋር አብሮ የሚሄድ ነው | | | | |
| 9 | በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የሚዘጋጁ የንባብ መልመጃዎች የማንበብ ክሂላቸውን ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው | | | | |
| 10 | ተማሪዎችን የምንባብ ልምድ ለማዳበር ግፊትና አገዛ ማድረግ አድካሚና አሰልቺ ነው | | | | |

# አባሪ ሐ

## ቅድመ ፈተና

## በጅማ ዩኒቨርስቲ

የማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብዕ ኮሌጅ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለቡልቡል 9ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ቅድመ ፈተና

የትምህርት ቤቱ ስም................................... ክፍል...............................

የተፈቀደዉ ሠዓት 20 ደቂቃ

ሙሉሰዉ ...ለወላጆቼ ሶስተኛ ልጅ ነኝ እናቴ በጣም ታሳዝነኝ ነበር ፤ የወደቀባትን ሀዘን መቋቋም አልቻለችም ነበር አካል ጉዳተኛ ሁኔ ስለተወለድኩ እኔን ስዉ እናዳያይባት ደበቀችኝ። ፅሀይ እስክትናፍቀኝ ድርስ ከቤታችን ጓዳ ተሸሸግሁ ። በርግጥ አባቴን ስዉ እንዲያየኝ አይፈልጉም ።እናታችን አንቱ ትላቸዉ ስለነበር ይመስለኛል ሁላችንም አንቱ የምንላቸዉ እኔ ግን አልወዳቸዉም ነበር። ስለማይወዱኝ ሁል ጊዜም ስለሚያማርሩኝ እሳቸዉ ባያዩኝ እመርጣለዉ ካዩኝ ቀኑን ሙሉ ምናልባትም ሌሊቱንም እኔን፤ ራሳቸዉን ፤እናቴንም ይርግማሉ ። ስድብ መአት ያዘንባሉ ። እነዚያ ካፋቸዉ የሚዘንቡ የምሬትና የርግማን ቃላት ልቤ ላይ ሲያርፉ ትንሷን ልቤ እንደ ፍም ይለበልባሉ። ካባቴ አንደበት ይወጡ የነበሩት እነዚያ ቃላት ዛሬም በሌሎች በኩል አልፈዉ የስንት ህፃናትን ልብ እንደሚያደሙ ቤት ይቁጠርዉ ።ዛሬስ ስንት አካል ጉዳተኛ ህፃናት ጨለማ ዉስጥ ቤት ተቆልፎባቸዉ ይሆን ? ስንቶቹስ ከስዉ ያነሱ ተደርገዉ ተጥለዉ ይሆን አሁንም ቤት ይቁጠራቸዉ። ወደጀመረኩት ታሪክ ልመለስና በልጅነቴ ግዜ ድሰታ የሚሰማኝ ከአባ ጋር ስሆን ነበር። አለችና በረዥሙ ተነፈሰች ።ቃላት የጠፏት ያህል ከንፈሮቿ በስሱ እየተላወሱ ዝም አለች። እድምተኛዉ ሁለንተናዉ ጆሮ ሆኖ ያዳምጣታል አንዳንዱ እያንዳንዱን ቃላት ከእየአንዳንዱ ቃላት ከእያንዳንዱ የቀለም ስንጥር ጋር እያሰናሰለ ለሚስጥር ድር ይፈትላል ከልጀነቷ ጀምሮ የብርሀን ፍቅር ያንገላታት ነበር ፤ ብቸኝነቷን የምትረሳዉ በበሩ ጭላንጭልሾልከዉ ከገቡ የብርሀን ጨረሮች ጋር ስትጫወት ነዉ በጀርባዋ ተንጋላ በጆቿ ጥላ ልዩ ልዩ ቅርፅ እየፈጠርች ትፍነከነካለች ። እጇን በበሩ ሽንቁር በሚገባዉ ጨርር መንገድ ላይ አስገብታ ጣቶቿን ስትሰበስብ አጠገቧ ያለዉ ግድግዳ ላይ የጇ ጥላ በአሳ ቅርፅ ይታያል ። ወዲያዉ ጣቶቿ ሲላወሱ የዉሻ ቅርፅ ይሆናል ...ደግሞ ሌላ ቅርፅ ... ። (ምንጭሰለሞን ታየ ፤ ሙሉሰዉ እና ሌሎች ፤2002 ፤1-19)

***መመሪያ አንድ፡-***

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እዉነት ወይም ሀሠት በማለት መልሱ*

…………1. የዚህ ታሪክ ባለቤት ለቤተሰቦቿ የመጀመሪያልጅ ነች፡፡

………….2. ባለታሪኳ ወላጅ አባቷን በጣም ትወዳቸዋለች፡፡

………….3. ባለታሪኳ ከልጅነቷ ጀምሮ እንደ ህጻናት ተጫዉታ አላደገችም፡፡

…………..4.ባለታሪኳ ከአባ ጋር ስትሆን በጣም ትደሰታለች፡፡

………….5.ልጅቷ በቀዳዳ ወደዉጭ ትመለከት የነበረዉ መንቀሳቀስ ስለማትችል ነዉ፡፡

***መመሪያ ሁለት፡-***

ከላይ በቀረበዉ ምንባብ መሰረትለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ

………….6. የባለታሪኳ እናት ልጇን ጓዳ ዉስጥ የደበቀቻት

ሀ.አካል ጉዳተኛ ስለሆነች ለ. ስለምታፍርባት ነዉ ሐ. ህመሙ የሚብስለመሰላት ነዉ

………..7.ባለታሪኳ በእጆቿና በብርሃን ጨረር ትጫወት የነበረዉ

ሀ.ብቸኛ ስለሆነች ለ. ሰዉ ስለማትወድ ሐ.ሁሉም መልስ ነዉ

……….8. የባለታሪኳ ልብ ፍም እንዳረፈበት ሁሉ የሚንገበገበዉ ሀ.በአባቷ ንግግር ለ.በጎረቤቱ አሽሙር ሐ.በራሷ ተፈጥሮ

……….9. ባለታሪኳ ምኝታዋ ሲያቃጥላት ምን ታደረጋለች? ሀ.ትሮጣለች ለ.ትቀመጣለች ሐ.የዉጭዉን ዓለም በቀዳዳ ትመለከታለች

………..10. ባለታሪኳ በጣቶቿ የምትሰራዉ ቅርጽ

ሀ.የዉሻ ለ.የድመት ሐ. የአይጥ

## አባሪ መ

ፍርድ አስተዳዳሪ ተብሎ በመንግስት እምነት የተጣለባቸዉ ሰዉ አደራ በልተዉ የሀገር የወገን ቅርስ ከምንም በላይበባእዳን መሬት ዉስጥ የተዳፈነ ሀብታችን መመዝበሩ ሳበቃአመድ ሰጥተዉ ወርቅ ለሚወስዱብን ባእዳን አንፅር ሀብታችን ለግል ጥቅሙ ሲሸጥ ፡ይህ ሁሉ ሳያንስ ራሱን በንፁህን ዉስጥ ሽጉጦ ፍርድ ቤቱን ጭምር ባዘጋጃቸዉ አፈ ጮሌዎችአሳሳተ ወንጀለኛ ቢሆን እንኳን በአግባቡ ለህግ ማቅርብ ሲቻል በአካሉ ላይ ዘግናኝና ከባድ ድብደባ አድረሶበት በሀኪም ማስርጃ መሰረት ተከሳሽ አቶ ይበልጣል እህል እንኳን ቆርሶ የሚጎርስበት እጅ የለዉም ፡፡ ይህ ሳያንስ በማረሚያ ቤት ዉስጥ መግደል ሙከራ ተደረገበት ከዚህም ሌላ ባድማ ጠባቂ በተባለዉ ልጁ ላይ በድጋሚ የግድያ ሙከራ ተደረገ፡፡ እነዚህም ሁሉ ክቡር ፍርድ ቤቱ ግንዛቤ ዉስጥ አስገብቶ ያቃቢ ህጉን የመፋረጃ ሀሳብም በማነፃፀር ተከሳሹን በነፃ ከመልቀቅ ባሻገር ለደርሰበት ጉዳት ሁሉ የሂወት ካሳዉንም እንዲከፈለዉ በመወሰን በተጠርጣሪዎቸሁ ላይ ትክክለኛዉና ርቱዕ የሆነ የፍርድ ዉሳኔ እንዲሰጥልኝ በትህትና እጠይቃዉ! ”በማለት ንግግሩን ፈፀመ፡፡

(ምንጭ ይስምአከ ወረቁ 2004 ተከርቸምና ሌሎች ገፅ 176)

መመሪያ አንድ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት የተሰመረባቸዉን ቃላት ፍቻቸዉን በመምረጥ መልሱ፡፡

…………1.<u>የሀገር ቅርስ</u> የሚለዉ ቃል በምንባቡ መሰረት ቀጥተኛ ፍቹ

ሀ.በጋራ ሊጠበቅ የሚችል የሀገር ንብረት ለ.የግል ንብረት ሐ.የቤተሰብ ንብረት

…………..2.<u>ወንጀለኛ</u> የሚለዉ ቃል በምንባቡ ያለዉ ቀጥተኛ ፍች

ሀ.አርአያነት የሌለዉ አስቀያሚ ስራን የሚሰራ ለ. ህግን የተላለፈ ሐ. ሰዎችን የሚንከባከብ መ. ሀናለ

……………3.<u> አፈ-ጮሌ</u> የሚለዉ ቃል በምንባቡ ዉስጥ ያለዉ ቀጥተኛ ፍች

ሀ. በሀሰት ተናግሮ የሚያሳምን ለ. ቶሎቶሎ የሚናገር ሐ. ሀናለ

…………….4.<u> ዘግናኝ</u>የሚለዉ ቃል ቀጥተኛ ፍቹ ከምንባቡ አንፃር

ሀ.ለማየትና ለመስማት ከባድ የሆነ ለ.አስቀያሚ ሐ.የሚያዝናና መ. ሀናለ

……………..5.<u> ባዕዳን</u>የሚለዉ ቃል ቀጥተኛ ፍች ከምንባቡ አንጻር

ሀ. ሀገር በቀል ያልሆነ ለ. ወገናችን የሆነ ሐ. የሌላ ሀገር ሰዉ መ.ሀናሐ

መመሪያ ሁለት ከላይ የቀረበዉን ፍርድ የሚለዉን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከክፍት ቦታዉ ሊገባ የሚችለዉን ቃል በተመሳሳይ ተኩ

ሀ.መመዝበር ለ.ከጥቅም ዉጭ ሐ.ጠባቂ መ.ከባድ ሠ.ቆርሶ

……………6.የገዛ ሀገራችን ንብረት በአላዋቂዎች ………… ዝም ብሎ መመልከት ተመልሶ ችግሩ ከኛዉ ራስ የማይዎርድ ይሆናል፡፡

…………….7.አንዳንዱ የለመደበት ሌባ…………..የሆኑትን ንብረቶች ሳይመለከት ተስበድብዶ ለመስረቅ ሲሞክር በቁጥጥር ስር ሲዉል ያስቀኛል፡፡

…………….8.የሀገርን ቅርስ መጠበቅ …………….. ሀላፊነት በመሆኑ መጠንቀቅ ያሻል፡፡

…………….9. አንዳንድ ባለሃብቶች የድርጅቶቻቸዉን ………….. በክብር ተንከባክበዉ ይይዛሉ ሌሎች ደግሞ ባጭር ጊዜ በባህሪ ማነስ ያሰናብቷቸዋል፡፡

………….10.ያለዉ ለሌለዉ የያዛትን …………..ማካፈል የደግነት መገለጫ